“ወነአምን በአሐቲ ጥምቀት ለሥርየተ ኀጢአት፣ ኀጢአትን በሚሰረይባት በአንዲት ጥምቀት እናምናለን”

ሃማኖተ አበው ፲፯፥፲፪

# ስምዐ ጽድቅ

## ማውጫ


፪ አጫጭር ዜናዎች

፬ መልእክት

፮ ሪፖርታዥ

፱ ቤተ አብርሃም

፲፪ ቃለ መጠይቅ

፲፭ የሕፃናት ዓምድ

፲፯ ትዝብት

፲፱ ምሥጢሬን ላካፍላችሁ




## ስምዐ ጽድቅ

የቤተ ክርስቲያኒቱን ትምህርተ ሃይማኖት፣ ሥርዓትና ትውፊት ጠብቆ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ማኅበረ ቅዱሳን በኅትመት ሚዲያ መምሪያ እየተዘጋጀ በወር ሁለት ጊዜ የሚወጣ መንፈሳዊ ጋዜጣ


ጳጉሜን ፭ ቀን ፲፱፻፹፭ ዓ.ም. ተጀመረ



☎ 011-1553555/ 011-1553442

✉ 80078

አዲስ አበባ

የዝግጅት ክፍሉ ኢሜይል
newspaper@eotcmk.org



ምክትል ዋና አዘጋጅ
ወርቅነሽ ቱፋ


ከፍተኛ ሪፖርተር
ካሣሁን ለምለሙ

ሪፖርተር
ምኒልክ ብርሃኑ

የገጽ መልክ (Layout) ዲዛይነርና
ጸሐፊ
ገነት ታደሰ



ብፁዕ አቡነ ፊሊጶስ የደቡብ ኦሞ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ እና የቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ዩኒቨርሲቲ የበላይ ኃላፊ



ብፁዕ አቡነ አብርሃም የባሕር ዳር ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ

# በቅድስት ቤተ ክርስቲያን ላይ እየተፈጸሙ ያሉ ሕገ ወጥ ተግባራት እንዲቆሙ ተጠየቀ

ካሳሁን ለምለሙ

አንዳንድ የመንግሥት አካላት በቤተ ክርስቲያን ላይ እየፈጸሙ ያሉትን ሕገ ወጥ ተግባርና ጠብ አጫሪ ድርጊት እንዲያቆሙ የደቡብ ኦሞ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስና የቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ዩኒቨርስቲ ዋና ኃላፊ ብፁዕ አቡነ ፊልጶስ ጠየቁ።

ብፁዕነታቸው ይህንን የጠየቁት በጃን ሜዳ በተከበረው የ፳፻፲፬ ዓ.ም በዓለ ጥምቀት ላይ ተገኝተው ባስተላለፉት አባታዊ መልእክት ነው። መንግሥት አንዳንድ ሀገራዊ አጀንዳን ለማስቀየስ በቤተ ክርስቲያን ላይ ድንጋይ መወርወርና ሰይፍ መምዘዝ ለምን እንደፈለገ የጠየቁት ብፁዕነታቸው "ትላንት በሀገሪቱ በሥልጣን ላይ የነበሩ አካላት በሕዝብ ተቃውሞ ከሥልጣናቸው እንደወረዱ ሁሉ ዛሬም በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ላይ ግፍና መከራ የሚያደርሱ አካላት በሕዝብ ከሥልጣናቸው ይወርዳሉም" ብለዋል። ቤተ ክርስቲያንና የክርስቶስ መስቀል ግን ለዘላለም ይኖራሉ ሲሉም አክለዋል።

ከዚህ ቀደም አንዳንድ የመንግሥት አካላት በቤተ ክርስቲያን ላይ ይሠሩ የነበረውን ግፍ ዛሬም ለመሥራት በዝግጅት ላይ ያሉ አካላት ካሉ ከድርጊታቸው እንዲቆጠቡ ብፁዕነታቸው አሳስበው ዛሬ ሥልጣን ላይ ያወጣቸው ሕዝብ መሆኑን የማይረዱ አንዳንድ የመንግሥት አካላት አላስፈላጊ ዋጋ እንዳይከፍሉ አስጠንቅቀዋል።

በተመሳሳይ ዜና የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በመንግሥት መዋቅር ውስጥ ባሉ ባለሥልጣናት ጽንፈኛ ተላላኪ ኃይሎቻቸው ከፍተኛ የሆነ በደል እየደረሰባት ዝምታን የመረጠችው መልካም ቀን እንደሚመጣ በማሰብ መሆኑን የባሕር ዳር ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ብፁዕ አቡነ አብርሃም ገልጠዋል። ብፁዕነታቸው ይህንን የገለጡት በባሕር ዳር ከተማ በተከበረው የጥምቀት በዓል ተገኝተው ባስተላለፉት አባታዊ ቃለ ምዕዳን ነው።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሀገርና የወገን ፍቅር ስላለት እሳትን በእሳት አጥፍታ የመጣው ይምጣ የማትል እንደሆነች የገለጡት ብፁዕነታቸው ዝምታዋ ግን የፍርሃት ሳይሆን በሀገራችን ሰላምና ፍቅር እንዲመጣ ከማሰብ የመነጨ እንደሆነም አክለዋል። ቅድስት ቤተ ክርስቲያን በምታከብራቸው የዐደባባይ በዓላት የሀገሪቱን "ስንደቅ ዓላማ ይዛችሁ አትውጡ" መባሉ እንዳሳዘናቸው ብፁዕነታቸው ገልጠው "የቅድስት ቤተ ክርስቲያን የበላይ አካል የሆነው ቅዱስ ሲኖዶስ በቤተ ክርስቲያን ላይ የሚደረሰውን እያንዳንዱን በደል በቅርበት እየተከታተለ ከጥላቻ ይልቅ ሰላምን፣ ፍቅርንና መረጋጋትን የሚሰብክ መሆኑ የቤተ ክርስቲያን ጠላቶች ትዕግሥትን ከፍርሃት ቆጥረው በቤተ ክርስቲያን ላይ ከጊዜ ወደ ጊዜ መከራ እያበዙባት ይገኛሉ" ብለዋል።

# ብፁዕ አቡነ ሚካኤል ዐረፉ

ምኒልክ ብርሃኑ



ብፁዕ አቡነ ሚካኤል የኢሉ አባቦራ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ

የኢሉ አባቦራ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ብፁዕ አቡነ ሚካኤል ከዚህ ዓለም በሞተ ሥጋ ተለዩ፡፡ ብፁዕ አቡነ ሚካኤል ከአባታቸው ከአቶ ወልደ አምላክ ሁንዴ እና ከእናታቸው ወ/ሮ በላይነሽ በድዮ በ፲፱፻፵፩ ዓ.ም በሰሜን ሸዋ ሀገረ ስብከት ሙከጡሪ ወረዳ በጅ ፊኔሊ ቀበሌ ልዩ ስሙ ደሴ በተባለ ሥፍራ ተወለዱ፡፡

ዕድሜአቸው ለትምህርት ሲደርስ በደብረ ሊባኖስ ገዳም መዝሙረ ዳዊት፣ ንባብና የቃል ትምህርትን ከመምህር ገብረ ማርያም፤ መዝገበ ቅዳሴን ከየኔታ ልዑል ተማሩ፡፡ በዚሁ ገዳም ጾመ ድጓ እና ድጓን አጠናቅቀው ዝማሬ መሥዋዕትን እያጠኑ ሳለ ለብሔራዊ ውትድርና ጥሪ ወደ ማሠልጠኛ ተቋም ገቡ፡፡

ብፁዕ አቡነ ሚካኤል የወታደራዊ ማሠልጠኛው ተቋም ከነፍሳቸው ጥሪ ጋር አብሮ የማይጓዝ በመሆኑ በእግዚአብሔር ፈቃድ ወደ ደብረ ሊባኖስ በመመለስ አቋርጠውት የነበረውን የአብነት ትምህርታቸውን እንደገና ቀጠሉ፡፡ በዚያም የአቋቋም መምህር ከነበሩት ከየኔታ ገብረ ሕይወት ዘንድ አቋቋምን የተማሩ ሲሆን ከየኔታ ምሕረት እና ከየኔታ ዐምዴ ደግሞ ቅኔን ተቀኝተዋል፡፡

ብፁዕነታቸው የነበራቸውን ትምህርት የበለጠ በማጠናከርም ከመምህር ጥበቡ አስናቀ መጻሕፍተ ብሉያትን አጥንተዋል፡፡ በትምህርታቸውም ባሳዩት ብልጫ በመምህራቸው ጥበቡ የጉባኤ ቤት ምክትል መምህር ሆነው እንዲያገለግሉ ተሹመዋል፡፡ በዚህ ሹመት መሠረት መጻሕፍተ ብሉያትን በማስተማር ጎን ለጎንም መጻሕፍተ ሐዲሳትን እየተማሩ ገዳሙን ለስምንት ዓመታት አገልግለዋል፡፡ በ፲፱፻፺፯ ዓ.ም በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ አማካይነት የደብረ ሊባኖስ ገዳም የመጻሕፍተ ብሉያት ዋና መምህር ሆነው ተሹመዋል፡፡

የቀድሞው አባ ኃይለ ሚካኤል ወልደ አምላክ የአሁኑ ብፁዕ አቡነ ሚካኤል ሐምሌ ፳፻፱ ዓ.ም በብፁዕ አቡነ ማትያስ አንብሮተ እድ ከተሾሙት ፲፭ ኤጲስ ቆጶሳት መካከል አንዱ በመሆን የኢሉባቦር ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ሆነው ተሹመዋል፡፡

ብፁዕ አቡነ ሚካኤል በሊቀ ጳጳስነት ከተሾሙ በኋላ በኢሉባር ሀገረ ስብከት መንፈሳዊ ትምህርት ቤት በመክፈት እና አገልጋይ ካህናትን በማሠልጠን በአገልጋይ ካህናት እጦት ሊዘጉ የነበሩ በርካታ አብያተ ክርስቲያናት አገልግሎታቸው እንዲቀጥል አድርገዋል፡፡ ብፁዕነታቸው በተሾሙ በአጭር ጊዜ ውስጥ ስብከተ ወንጌልን በማስፋፋት እና የተለያዩ የልማት ሥራዎችን በማከናወን ላይ ሳሉ ባደረባቸው ሕመም ምክንያት በተለያዩ ሆስፒታሎች በሕክምና ሲረዱ ቆይተው በተወለዱ በ፸፫ ዓመታቸው ጥር ፱ ቀን ፳፻፲፬ ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋል፡፡

የቀብር ሥነ ሥርዓታቸውም ጥር ፲፮ ቀን ፳፻፲፬ ዓ.ም. ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ማትያስ ቀዳማዊ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም ወእጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት፣ ብፁአን አበው ሊቃነ ጳጳሳት፣ የመንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ጽ/ቤት ኃላፊዎች፣ የኢሊባቡር ሀገረ ስብከት ኃላፊዎችና ምእመናን በተገኙበት በደብረ ሊባኖስ ገዳም ተከናውኗል፡፡

# ወጥነት ያለው መዋቅራዊ አሠራር ቅድስት ቤተ ክርስቲያንን ከሚደርስባት ተፅዕኖ ለመታደግ

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን ሕልውና የሚፈታተኑ በርካታ እኩያት ድርጊቶች በዘመናት ውስጥ ሲፈራረቁ ኑረዋል:: የተከበሩና የተቀደሱ የእምነት ቦታዎቿን በማፍረስ፣ በማቃጠል፣ በመዝረፍና ቅርስ አልባ በማድረግ፣ የአምልኮ ቦታ እንድታጣ በየዘመናቱ የተነሡ አጽራረ ቤተ ክርስቲን የየራሳቸውን ጥረት ሲያደርጉ ቆይተዋል፤ ይህ ደግሞ በከፊልም ቢሆን ተሳክቶላቸዋል:: አለፍ ሲሉም የቤተ ክርስቲያንን ልጆች በማገድ፣ በማሳደድ፣ በማፈናቀል፣ የክርስቲያኖችን ቊጥር ለመቀነስ ብሎም ለማጥፋት ያልወጡት ተራራ ያልወረዱት ቁልቁለት የለም:: ይህ አልበቃ ብሎ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን የአምልኮ ሥርዓት የምታካሂድባቸውን ዋና ዋና የዐደባባይ ይዞታዎች በአንድም በሌላም ምክንያት እያሳበቡ ሲነጥቁ፣ ድንበር ሲገፉ ኖረዋል፤ ዛሬም በቅድስት ቤተ ክርስቲያን ላይ እየተካሄደ ያለው እኩይ ዘመቻ አልቆመም::

ትላንት በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች የሚገኙ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አማኞች ከተወለዱበት እና ከኖሩበት መንደር እንዲፈናቀሉ፣ እንዲሰደዱ ተደርገዋል:: አብያተ ክርስቲያናት ያለምንም ከልካይ እንዲቃጠሉ፣ ካህናት አባቶች እንዲታረዱ በሕይወት የተረፉትም አካባቢያቸውን ለቀው እንዲሰደዱ ተገደዋል:: የተሰደዱትም ወደ መንደራቸው ሳይመለሱ፣ የተቃጠሉት አብያተ ክርስቲያናት በወጉ ተሠርተው ሳያልቁ፣ የብዙዎቹ ወገኖቻችን ደም ሳይደርቅ፣ ዛሬም ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ለሌላ መስቀል ታጭታ መከራዋን እያየች ነው::

በዚህ ‹‹ኦርቶዶክስ ተኮር›› በሆነው ጥቃት ውስጥ ጠላቶቿ ብዙዎች ናቸው:: የቤተ ክርስቲያቱን እምነት፣ ዶግማና ሥርዓት መቀየር የሚፈልጉ፣ ሀገርን እንደ ሀገር እንድትቆም ያደረገችውን ይህችን ቀዳማዊት ቤተ ክርስቲያንን ፈጽሞ ለማጥፋት ከልብ የሚሹ፣ የቤት ልጅ መስለው በስም የራሳቸውን አጀንዳ እና ፍላጎት ለማሳካት እርስ በርስ የሚሻኮቱ፣ በሀገር ታሪክ ውስጥ ያላትን ከፍ ያለ የልዕልና ቦታ ላለማየት በቅናት የታወሩ ከብዙዎቹ ጥቂቶቹ ናቸው:: እነዚህ የተለያየ ዓላማና አጀንዳ ቢኖራቸውም ቤተ ክርስቲያንን በማፍረስ ጉዳይ ተስማምተው እና ተቀናጅተው በሥርዓት እየተናበቡ የሚሠሩ መሆናቸውን በውል ተገንዝቦ በዚያ ልክ ቤተ ክርስቲያንን ለመታደግ መንቀሳቀስ አስፈላጊ ነው::

የቤተ ክርስቲያን ፈተና በነበረ እና በሆነ መሀል የሚቀር ሳይሆን በተሻለ እኩይ ሤራ፣ በተሻለ እና በተቀናጀ አሠራር ወደፊትም የሚቀጥል፤ ቤተ ክርስቲያንን ለባለ ውስብስብ ፈተናና ችግር የሚዳርጋት መሆኑን ሁሉም ሊገነዘበው የሚገባ ዓቢይ ጉዳይ ነው:: በመሆኑም ይህን የተቀናጀ፣ የተናበበና አልፎ አልፎም መዋቅራዊ በሚመስል መልኩ እየተካሄደ ያለውን ቤተ ክርስቲያንን የማዳከም ሥራ (ሤራ) ከሥሩ ነቅሎ ለመጣል ሁሉም የበኩሉን ድርሻ ሊወጣ፣ እንደቤተ ክርስቲያን ልጅ በአንድነት መቆም አስፈላጊም ወቅቱም የሚጠይቀው ነው::

ወቅት እና ምቹ ጊዜን ጠብቆ ቤተ ክርስቲያንን ለማዳከም ብሎም የቤተ ክርስቲያንን ይዞታዎች ለመንጠቅ የሚደረገውን ጥቃት ለማስወገድ የሚያስፈልገው የአንድ ሰሞን ጩኸትና ግርግርታ ሳይሆን በረጋና በሰከነ መንፈስ የሚደረግ እንቅስቃሴ ነው:: በተናጠል ሳይሆን በአንድነት፤ ብለው ነበር ለመባል ብቻ ሳይሆን በእኔነት ስሜት መነሳትና ዘላቂ መፍትሄ መፈለግ ተገቢ ነው:: ችግሮች ከተፈጠሩ በኋላ በዩቲዩብ በማራገብ የገንዘብ

መሰብሰቢያ እና የራስ ጥቅም ማጋበሻ እንዲሁም ዝናን መሰብሰቢያ ከማድረግ ይልቅ እንደ ቤተ ክርስቲያን ልጅ ቆም ብሎ ማሰብ ዘላቂ መፍትሄ ላይ እንደ አንድ ቃል ተናጋሪ እንደ አንድ ሐሳብ አሳቢ ሆኖ መወያየት ተገቢ ነው፡፡

ትላንት ቤተ ክርስቲያን እንድትሰደድ የተሠሩ ሥራዎች መልካቸው ለወጥ አድርገው ዛሬም በተመሳሳይ ቤተ ክርስቲያንን ሲያደሙ፣ ካለችበት ከፍታ ዝቅ እንድትል ባገኙት አጋጣሚዎች ሁሉ ሲሠሩ ለምን? እንዴት? ብሎ መጠየቅ ተገቢ ነው፡፡ መልኩን እየለዋወጠ ለመጣው የቤተ ክርስቲያን ጥቃት እንደትላንቱ ጮኾ ብቻ ማቆም፣ የአንድ ሰሞን ብቻ ማድረግ ጠላትን ለነገ የከፋ ጥቃት የሚያዘጋጅ ነውና ዘመኑን ዋጅቶ በማስተዋል ከጠላት በልጦ መገኘት ያስፈልጋል፡፡ ቤተ ክርስቲያንን ለከፋ አደጋ ለመዳረግ አማኝ ነኝ የሚለው ከማያምነው ጋር ሲስማማ አንድ እምነት ያለን እኛ የቤተ ክርስቲያን ልጆች ለአንድ ዓላማ እንዴት መቆም እንዳለብን የተማርንበት የታሪክ አጋጣሚ ነውና ሁሉም ሊነቃ ይገባል፡፡

ቤተ ክርስቲያን ትላንት ከተፈጸመባት ቊስል እንድትሽር፣ ነገ ሉአላዊነቷ ተጠብቆ እንዲቆይ እርስ በርሱ የሚናበብ፣ ለራሱ ሳይሆን ለቤተ ክርስቲያን ክብር የቆመ ልጅ ያስፈልጋታል፡፡ አባቶችን የሚያከብርና የሚሰማ፣ ምክርን የሚቀበልና የሚፈጽም የቤተ ክርስቲያንን ጉዳይ ግለሰባዊ ሳይሆን ተቋማዊ አድርጎ የሚሠራ መዋቅራዊ አደረጃጀት ወሳኝ ነው፡፡ ከፌስ ቡክና ከዩቲዩብ ባለፈ በተግባር የተገለጸ ክርስትና፣ ቤተ ክርስቲያንን ሊታደግ የሚችል ቁመና ይዞ መገኘት አስፈላጊ ነው፡፡

የትም ቦታ በየትኛውም ጊዜ በቤተ ክርስቲያን ላይ የሚፈጸሙ ጥቃቶች የዚያ አካባቢ ብቻ ሳይሆን የመላው ኦርቶዶክሳውያን ጥቃት ነውና በዚያ ልክ መታሰብ አለበት፡፡ ሁል ጊዜ ከየትኛውም አካል በየትኛውም ቦታ የጥቃት ሰለባ የሆነቸው ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችንን በቋሚነት ከሚደርስባት ጥቃት ሁሉ ለመታደግ ሁሉም የቤተ ክርስቲያን ልጆች የየድርሻቸውን ሊወስዱ ይገባል፡፡ ምእመናን እንደልጅነታቸው በቤተ ክርስቲያኒቱ መዋቅር ውስጥ በመታቀፍ እና ከአባቶች የሚሰጡ ትእዛዞችንና መመሪያዎችን በመተግበር እንደየድርሻቸው ሊሠሩ ይገባል፡፡ የቤተ ክርስቲያን አባቶችም ከላይ ከቤተ ክህነት ጀምሮ እስከ አጥቢያው ድረስ በተዘረጋው መዋቅር አማካኝነት ወጥ የሆነ መልእክትን በማስተላለፍ እና ዘላቂ የሆነ መፍትሔ በማበጀት ቤተ ክርስቲያን ከተቃጣባት አደጋ ሊታደጓት ይገባል፡፡

በአጠቃላይ በተጠና መልኩ በቤተ ክርስቲያን ላይ እየተካሄደ ላለው የቤተ ክርስቲያን ጥቃት መዋቅራዊ አደረጃጀት፣ የእዝ ሠንሰለቱን የጠበቀ ተግባቦት እና ሥራ ከቤተ ክህነት የሚጠበቅ ሲሆን መንግሥትም እንደ መንግሥት የሀገርን ሰላም ሊያደፈርሱ የሚችሉ መሰል ጥፋቶችን አስቀድሞ በመከላከል የቤተ ክርስቲያንን ሕልውና የሀገርን ሰላም ማስጠበቅ ተቀዳሚ ድርሻው ሊሆን ይገባል፡፡

# በጥምቀት በዓል በበጎ ፈቃድ የሚያገለግሉ ወጣቶች የአገልግሎት ትሩፋትና ሥጋት

ሻምበል ጥላሁን

ዲያቆን ሰሎሞን ዮሐንስ ‹‹የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ወርቃማ ዘመናት›› በሚለው መጽሐፋቸው እንዲሁም ሙሐዘ ጥበባት ዲያቆን ዳንኤል ክብረት "ስማችሁ የለም" በሚል ርእስ ባሳተሙት መጽሐፍ ‹‹የመጥምቃውያን ቱሩፋቶች›› በሚለው ጽሑፋቸው እንደሚያስረዱት በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ውስጥ ክሥተቶች ዘመን፣ ዘመን አላቸው።

ሙሐዘ ጥበባት ዲያቆን ዳንኤል ክብረት በዚህ መጽሐፋቸው በገጽ ፸፱ ላይ እንደሚያስረዱት ‹‹ከ፲፱፻፵ ዓ.ም እስከ ፲፱፻፷ ዓ.ም ባሉት ዘመናት ማኅበራት በመላው ሀገራችን በብዛት የወጡበትና እንደ ብርቅም የታዩበት ዘመናት ነበሩ። ያንጊዜም በየአጥቢያው የነበሩት የወጣት ማኅበራት እንጂ ሰንበት ትምህርት ቤቶች አልነበሩም። ከ፲፱፻፷ዎቹ በኋላ የባሕታውያን ዘመን መጣ። ከገጠር እስከ ከተማ ሰንሰለት የታጠቁ፣ አዳፋ የለበሱ፣ መቁጠሪያ ያነገቱ፣ በባዶ እግራቸው የሚሄዱ፣ መስቀል ከሰላጢን የያዙ ባሕታውያን ኢትዮጵያን ሞሏት›› ይላሉ።

ከ፲፱፻፷ዎቹ አጋማሽ እስከ ከ፲፱፻፸ዎቹ የሰንበት ትምህርት ቤቶች ዘመን መጣ። በየአጥቢያው፣ በገጠሩ፣ በከተማው ሰንበት ትምህርት ቤቶች የማኅበራቱን ቦታ ተክተው ወጡ ይላሉ ድርሳናቱ። ከ፲፱፻፷ዎቹ እስከ ከ፲፱፻፹ዎቹ መጀመሪያ ድረስ ጽኑዓን ሰባክያን ዘመን እንደነበርም ይጠቅሳሉ። በዚህ ዘመን የነበሩ ሰባኪያን ኮምኒዝምን ተጋፍጠው ወንጌልን በማስተማር ወጣቱን እንዳተረፉትም ሙሐዘ ጥበባት ዲያቆን ዳንኤል ክብረት ያስረዳሉ።

ከ፲፱፻፹ዎቹ አጋማሽ ጀምሮ ደግሞ የ‹‹ባሕታውያኑ›› ዘመን ዳግም መጣ። በዚህ ዘመን ራእይ ታየን እያሉ ሕዝቡን ባንዲራ እያስለበሱ ባሕታውያንን አለመከተል ክርስቶስን አለመከተል እስኪመስል ድረስ በባዶ እግር እንድሄድ አስደገደጉት።

ትንሽ ቆየት ብሎም የዝዋያውያን ዘመን እንደመጣም ሙሐዘ ጥበባት ዲያቆን ዳንኤል ይገልጻሉ። በዚህ ዘመንም በብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ አማካኝነት በዝዋይ ሐመረ ብርሃን ቅዱስ ገብርኤል ገዳም የተጀመረው የሰባክያነ ወንጌል ሥልጠና ውጤታማ በሆኑ ወጣት ሰባክያን በመላው ሀገራችን ለስብከተ ወንጌል መፋጠን መሠማራታቸውን ጽሑፎቹ ይጠቁማሉ። በዚሁ ጊዜ ከቤተ ክህነቱ መጽሔቶችና ጋዜጦች ወጣ ያሉ መንፈሳውያን መጽሔቶችና ጋዜጦች ብቅ ብቅ አሉ። የሠራተኛ ጉባኤያትም በየመሥሪያ ቤቱ ተቋቋሙ።

በ፲፱፻፺ዎቹ አጋማሽ ደግሞ ስብከትን አንዱ መተዳደሪያቸው ያደረጉ 'የግል ሰባክያን' እና 'ዘማርያን' ወደ ሕዝቡ መጡ። የትምህርትና የስብከት ካሴቶችም በከተማውና በገጠሩ ናኙ፤ ይህም የትምህርተ ወንጌልንና የመዝሙር አገልግሎቶችን ተደራሽነት እያሰፋው መጣ። ይሁን እንጂ በዚህ ዘመን ከትምህርቱ ይልቅ ሰባኪው፤ ከመዝሙሩ ይልቅ ዘማሪው እየታወቀ ችግር ሆኖ እንደነበርም ጽሑፎቹ ያስረዳሉ። የቤተ ክርስቲያን የታሪክ ተመራማሪዎች የጻፏቸው ጽሑፎች እንደሚገልጹት ከ፲፱፻፹ዎቹ አጋማሽ ደግሞ እንደገና የሰባክያኑ እና የዘማርያኑ ማኅበራት ዘመን ተከሠተ።

በየአካባቢውም በርካታ የጽዋ፣ የጉዞ፣ የነዳያን መጋቢ፣ የገጠር አብያተ ክርስቲያናትን አሠሪ፣ የተጎዱ ገዳማትን መርጃ የሚሉ ማኅበራት ተሰየሙ።

ከ፷፯ ዓ.ም በኋላም ለአጭር ጊዜም ቢሆን የአዳራሽ ጉባኤያት ዘመን መጥቶ እንደነበር ጽሑፎቹ ያስረዳሉ። ለአጭር ጊዜ የቆየው ይህ ዘመን፤ ጉባኤያት ከቤተ ክርስቲያን ቅጽር ወጥተው ወደ አዳራሽ እንዲያመሩ እያደረገ፣ ጉባኤያትን ከገቢ ማሰባሰብ ጋር እያዛመደ፣ የሰባክያኑንና የዘማርያኑን ስም በየማስታወቂያ ቦርዱ በመለጠፍ ገበያን የተሻማበት ዘመን እንደነበርም የጥናት ጽሑፎቹ ይጠቁማሉ።

በጥምቀት በዓል በበጎ ፈቃድ የሚያገለግሉ ወጣቶችም የመጡት በዚህ ዘመን መካከል ነበር። በዚህ ጽሑፍ ወጣቶቹ ወደ አገልግሎቱ በመምጣታቸው ምን ትሩፋት አገኙ? ወጣቶቹ እንደአመጣጣቸው በቤተ ክርስቲያን አስተዳደራዊ መዋቅር ውስጥ ባለመደራጀታቸው የሚኖረው ሥጋትስ ምንድን ነው? ስንል እንጠይቃለን።

ወጣት ሸዋለም ወልዴና ወጣት እርሱባለው አብሸሮ በደብረ መዊዕ ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን ቅጽር ግቢ ውስጥ የአካባቢውን ወጣቶች ሰብስበው ይወያያሉ፤ ለሠርክ ጸሎት ወደ ቤተ ክርስቲያኑ የሚመጡ ምእመናን ሁሉ እነዚህን ወጣቶች በስስት እየተመለከቱ ጸሎቱን ያደርሳሉ። ምእመናን እነዚህን ወጣቶች በስስት የሚመለከቱት በቤተ ክርስቲያን ቅጥር ውስጥ በመገኘታቸው ብቻ አይደለም፤ ትናንት በአካባቢው ቆመጥ ይዘው የሚደባደቡ፣ ጩቤ ይዘው የሚወጉ ወጣቶች ዛሬ አደብ ገዝተው በቤተ ክርስቲያን ዐውደ ምሕረት በመገኘታቸው እና ትናንት ምእመናንን ለመላከፍና ለመዝረፍ ወደ ቤተ ክርስቲያን የሚሄዱት ወጣቶች፤ ዛሬ ግን ያንን ክፉ ጠባይ ትተው፣ በቤተ ክርስቲያን ቅጽር ውስጥ ተገኝተው በጽሞና ተሰብስበው ስለ አገልግሎት ሲወያዩ በማየታቸው ነው እንጂ።

ወጣት ሸዋዓለም ወልዴ አዲሱ ሚካኤል እየተባለ በሚጠራው የደብረ መዊዕ ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን አጥቢያ የሚገኘውን የወጣቶች ማኅበርን ለ፲፩ ዓመታት በሰብሳቢነት ማገልገሉን ይገልጻል።

ስለ በጎ ፈቃድ አገልግሎት ሰጪዎቹ ወጣቶችም ሲናገር ‹‹ዛሬ በቤተ ክርስቲያን ተሰብስበው የምንመለከታቸው ወጣቶች ትናንት የአካባቢው ሰው ሁሉ በስጋት የሚመለከታቸው፣ ዛሬ ግን በክርስትናቸው ጸንተው፣ በምግባርም ታርመው፣ በዓላትንና ጉባኤያትን በማድመቅ የሚያገለግሉ የቤተ ክርስቲያን ጌጦች ሆነዋል። እነዚህ ወጣቶች በዓላትና ጉባኤያትን በድምቀት እንዲከበሩ ከማገልገል በተጨማሪ በርካታ የበጎ አድራጎት ሥራዎችን ይሠራሉ፤ ወጣቶቹ ከኪሳቸው ከሚያወጡትና በአካባቢው ከሚገኙ ምእመናን በሚሰበስቡት ገንዘብ በገጠር የሚገኙና ተዘግተው የነበሩ አብያተ ክርስቲያናትን ከማስከፈት አልፈው አዲስ ቤተ ክርስቲያን እንዲሠራም አስተዋጽኦ ያደርጋሉ፤ በአካባቢው የሚገኙና ወላጆቻቸው በተለያዩ ምክንያት የሞቱባቸውን ሕፃናት በመመገብ፣ አረጋውያንንም በመንከባከብ ይታወቃሉ›› በማለት ያክላል።

ወጣቶቹ በዚህ አገልግሎት በመሳተፋቸው ወደ ቤተ ክርስቲያን ቀርበው ቃለ እግዚአብሔርን በመስማታቸውም ቀድሞ ከነበራቸው ክፉ ጠባይ በንስሓ የተመለሱና የቈረቡ፣ በቍርባንም ያገቡ በርካቶች መሆናቸውን የሚናገረው ወጣት ሽዋዓለም ከዚሁ አያይዞ የእርሱን ሕይወት እንደ አብነት ሲያስረዳ ‹‹እኔ ተደባዳቢና ወደ ቤተ ክርስቲያን የሚሄዱ ምእመናንን የማንጓጥጥ አስቸጋሪ ሰው ነበርኩ፤ አሁን ግን በዚህ አገልግሎት በመሳተፌ ንስሓ እንድገባና በመርካቶ ቅዱስ ራጉኤል ቤተ ክርስቲያን በሚሰጠው የነገረ ሃይማኖት ትምህርት ራሴን በማነፅ አሁን በአጥቢያዬ በደብረ መዊዕ ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን ሰንበት ትምህርት ቤት በሚሰጠው ተከታታይ የነገረ ሃይማኖት ትምህርት በማስተማር እሳተፋለሁ። የዛሬ ፲፬ ዓመት ወደ አገልግሎቱ ስንመጣ ብዙ ዓይኖች ወደ እኛ ያማትሩ ነበር፣ ተከታታይ የነገረ ሃይማኖት ትምህርት ያስተምሩን፣ የሠርክና ወርኃዊ ጉባኤያትንም ይዘጋጁልን ነበር›› የሚለው ሽዋዓለም ቀስ በቀስ እነዚህ ድጋፎች በመቅረታቸው ከ፳፻ በላይ የነበሩት አባላት አሁን ላይ ወደ ፻፶ ዝቅ ማለታቸውን ያስረዳል። ከዚህም ሌላ በንስሓ የተመለሱ እንዳሉ ሁሉ ወደ ቀደመ በደላቸው የተመለሱ ወጣቶች እንዳሉም ይናገራል።

ከዚሁ አያይዞም ‹‹ከኢትዮጵያ ዕሥራ ምእት በኋላ የጥምቀት በዓልን ተከትሎ ወጣቱ ወደ ቤተ ክርስቲያን ለመመለስ ያሳየው ፍላጎት፣ ተነሣሽነትና የአገልግሎት ትጋት በሁሉም የቤተ ክርስቲያን ልጆች ልቡና ውስጥ ትልቅ ተስፋን ያሳየ ነበር›› የሚለው ሽዋዓለም ‹‹ኋላ ግን ወደ ቤተ ክርስቲያን የመጡትን ወጣቶች ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ባላት መዋቅር ማንም ስላላደራጀን፣ በወረት የተሰጠን ትኩረትም ስለቀረ ወጣቱ እየተነሣ ማኅበር መመሥረት ያዘ›› በዚህም ‹የእገሌ ወእገሊት ማኅበር› እየተባሉ ያለ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ፈቃድ ተቋቋሙ። በርካታ ማኅበራትም በማኅበራት ስም ለግል ጥቅም ማጋበሻነት ሊውል የሚችል ገንዘብ እየሰበሰቡ ለቤተ ክርስቲያን አደጋና ችግር ፈጣሪዎች እየሆኑ መጥተዋል›› ሲል ይናገራል።

በመቀጠልም ‹‹ቀደም ሲል ለመግለጽ እንደሞከርነው እነዚህን ወጣቶች በሰ/ት/ቤቶች በኩል አስተምሮ ወደ መደበኛ አገልግሎት ለመቀላቀል ከፍተኛ ፍላጎትና ጥረት ነበር›› የሚለው ወጣት ሽዋዓለም ‹‹በዚህ ላይ በዘላቂነት ስላልተሠራና ትኩረት ስላልተሰጠው ማኅበራቱን በሰ/ት/ቤቶች በኩል አስተምሮ ወደ መደበኛ አገልግሎት የማምጣቱ ጉዳይ መክኖ ቀርቷል። የአንዳንድ አብያተ ክርስቲያናት አለቆችም ከሰንበት ተማሪዎች ጋር አልስማማ ሲሉ የወጣቶቹን ማኅበራት እንደማስፈራሪያ መጠቀም ጀምረዋል፤ እንዲህ ዓይነቱ አካሄድ በቶሎ ካልተቀረፈ አደጋው የከፋ ሊሆን ይችላል። ቤተ ክርስቲያን እነዚህን የጥምቀት በዓል የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ሰጪ ወጣቶች ባሏት መዋቅሮች ውስጥ ሥርዓት ሠርታ ካላቀፈች በርካታ ችግሮች ሊከሠቱ ይችላሉ።›› በማለትም ያክላል።

ወጣት ሸዋለም ‹‹ከሚከሠቱት ችግሮችም የመጀመሪያው ማንም አዲት የማያደርገውና የገጠር አብያተ ክርስቲያናት ማሠሪያ፤ ለጥምቀትና ለተለያዩ በዓላት ማክበሪያ በሚል ሰበብ ከሀገር ውስጥ እስከ ውጪ ካሉ ምእመናን የሚሰበሰበው ገንዘብ ለግል ጥቅም የሚውልበት አጋጣሚ ይፈጠራል የሚለው ወጣቱ። ሁለተኛው ስጋቱ ደግሞ እነዚህ ወጣቶች በአብዛኛው የቅድስት ቤተ ክርስቲያንን ዶግማ፣ ቀኖናና ትውፊት ያልተማሩ በመሆናቸው በቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ላይ ሲሳተፉ ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያንን የሚጥሱ ወደ ቤተክርስቲያን ለሚመጡ ታዳጊዎችና ወጣቶች አርአያነታቸው ዝቅ ያለ እንዳይሆን፤ ወጣቶቹ ያሉበት የሥርዓት ቤተ ክርስቲያን ግንዛቤ ጉድለት በቤተ ክርስቲያን የተፈቀደ እስኪመስል ድረስ ለሥርዓተ ቤተክርስቲያን የማይገዛ ፍሬ አልባና መራራ ትውልድ እንዳይተካ የሚል ስጋትም አለኝ›› በማለት ይናገራል።

ወጣት ሽዋዓለም ሦስተኛ ያለውን ችግር ሲገልጽም ‹‹በአንዳንድ አብያተ ክርስቲያናት የሥነ ምግባር ጉድለት የታየባቸውን አንዳንድ የሰ/ት/ቤት አባላት በሕጉ መሠረት ለማስተካከል ሲሞከር በማኩረፍ በቂ ክትትል ወደ ማይደረግባቸው ወደ እነዚህ የማኅበራት ኅብረት ሄደው መሸሸግ እየተለመደ መጥቷል። ከዚህም አልፎ በአንዳንድ አጥቢያዎች ሰንበት ት/ቤትን ያገለለ የሰብከተ ወንጌል ጉባኤ እስከ ማዘጋጀት ተደርሷል። ይህም ከቃለ ዐዋዲው ውጪ በሆነ መንገድ ሁለት የተለያዩ ሥርዓቶችን የሚያራምዱ፣ ሁለት የተለያዩ መዋቅሮች ያሏቸውና በጎሪጥ የሚተያዩ ወጣቶች በአንድ አጥቢያ እንዲኖሩ እስከማድረግ ደርሷል። በዚህ ምክንያትም በተለያዩ አድባራት በሁለቱ የወጣቶች ስብስብ መካከል ግጭቶች ሲፈጠሩ ይስተዋላል። ወደፊት ደግሞ ይሄ ግጭት ተባብሶ ወደ አላስፈላጊ ነገር ሊያመራ ስለሚችል የሚመለከተው ክፍል ይህን ከቃለ ዐዋዲው ውጪ ያለ አካሄድ በእንጭጩ ሊያርመው ይገባል›› ይላል።

ሌላው ስጋቱን የሚገልጸው ወጣት ረታ ገብረማርያም በአቃቂ መንበረ ሕይወት መድኃኔ ዓለም አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን የተቋቋመው የኤማሁስ የጥምቀት በዓል በበጎ ፈቃድ የሚያገለግሉ ወጣቶች ማኅበር ሰብሳቢ ነው። ወጣት ረታ የወጣቶችን የበጎ ፈቃድ አገልግሎት አስመልክቶ ሲናገር ‹‹የማኅበሩ አባላት እንደ አብዛኛው ከዚህ ቀደም በሠርክ ጉባኤያትም ሆነ በሰንበት ትምህርት ቤት ተምረው የማያውቁ፣

ከመንፈሳዊነታቸው ይልቅ በአስቸጋሪ አመላቸው የሚታወቁ የነበሩ ወጣቶቹ በቤተ ክርስቲያን አገልግሎት መሳተፍ በመጀመራቸው የቀደመውን ክፉ አመላቸውን በመተው ንስሓ ገብተው በቅዱስ ቊርባን ያገቡና ለማግባት እየተዘጋጁ ያሉም በርካቶች ናቸው። በማኅበራችን በአገልግሎትና በመንፈሳዊ ሕይወታቸው የጸኑትና ያልጸኑት ወጣቶች እየተለዩ መንፈሳዊ ሕይወታቸው የሚበረታበት ድጋፍ እየተደረገላቸው ነው›› የሚለው ሰብሳቢው አያይዞም ‹‹የማኅበራችን አባላት ቤተ ክርስቲያን ባላት መዋቅር ባይደራጁም ከደብሩ ሰበካ ጉባኤ እና ሰንበት ትምህርት ቤት ጋር ጥሩ መግባባት ስላለን በደብሩ ሰንበት ትምህርት ቤት አማካኝነት ተከታታይ የነገረ ሃይማኖት ትምህርት እንዲማሩ እያደረግን ነው›› ይላል።

ማኅበራቸውም በየዓመቱ ከሚከበረው የጥምቀት በዓል በተጨማሪ ቤተ ክርስቲያን በሚኖራት መርሐ ግብር ሁሉ አባላቱን አስተባብሮ ቀድሞ በመገኘት የሚጠበቅበትን አገልግሎት እየሰጠ እንደሚገኝ የሚገልጸው ወጣት ሸዋለም ‹‹በጥምቀት ዝግጅትም ሆነ በሌሎች የቤተ ክርስቲያን መርሐ ግብሮች ላይ የማኅበራችን አባላት በሚያስተናግዱበት ወቅት ወጥነት ያለውና ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያንን የተከተለ አለባበስ እንዲለብሱ እናደርጋለን፤ ይህ ሲባል ግን ከማኅበራችን አባላት የአለባበስ ሥርዓት የተለየ የሚለብሱና በፀጉር አቆራረጥና አያያዝ ችግር ያለባቸው አንዳንድ አባላት የሉም ማለት አይደለም›› ይላል።

ከዚህ በመቀጠልም ‹‹እነዚህን በሥነ ምግባር ወጣ ያሉትን አባላት በማስተማርና በአባቶች ካህናት በማስመከር ከስሕተታቸው እንዲታረሙም እናደርጋለን›› የሚለው ሰብሳቢው ‹‹በማኅበራችን ለጥምቀት ክብረ በዓል ማክበሪያ ለሚያገለግሉ ቁሳቁሶች መግዣ እና ነዳያንን ለመመገብ በአባላቱ ከመእመናን የሚሰበሰቡ ገንዘቦች የሚሰበሰቡት ከሰበካ ጉባኤ በሚሰጠን ማሕተም ባለው ወረቀት ነው›› ሲልም ይናገራል።

የማኅበራቸው አባላትና ማኅበራቸው በአንፃራዊነት ጸንተው የቆየዩትና ተከታታይ የነገረ ሃይማኖት ትምህርቱም ሳያቋርጥ ለአባላቱ እንዲሰጥ እያደረገ ያለው ከሰበካ ጉባኤውና ከሰንበት ትምህርት ቤቱ ጋር ባለው መግባባትና ቅርርብ መሆኑን የሚገልጸው ወጣት ረታ ደግሞ ‹‹ይህ ግንኙነት በሆነ አጋጣሚ ቢሻክር እንደ መሰል ማኅበራት በዓመት አንድ ጊዜ ብቻ ለጥምቀትና ለክብረ በዓላት ስንፈለግ መጠራታችን አይቀርም ግን አገልግሎታችን የሚፈለገውና ወጣቶቹም መንፈሳዊ ትምህርት እንዲያገኙ የሚደረገው በበጎ የደብር አለቃና በመልካም የሰንበት ትምህርት ቤት አመራር ፈቃድ ብቻ ከሚሆን ቤተ ክርስቲያን መዋቅሯን አስተካክላና ማኅበራቱን አቅፋ የምታስተዳድርበትን መፍትሔ መፈለግ ይኖርባታል›› ይላል።

ወጣት ዘካርያስ ጸጋዬና ወይዘሮ አዜብ ታደሰም የአቃቂ መንበረ ሕይወት መድኃኔዓለም አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ምእመናን ናቸው። እነርሱም በተመሳሳይ ስለ ጥምቀት በዓል በበጎ ፈቃድ የሚያገለግሉ ወጣቶች ያላቸውን ተስፋና ሥጋት ይናገራሉ።

ወይዘሮ አዜብ ከበደ በአቃቂ መንበረ ሕይወት መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን ታቦት አጅበው ወደ ባሕረ ጥምቀት በመሄድ የጥምቀትን በዓል ሲያከብሩ ከ፳ ዓመት በላይ እንዳሳለፉ ይገልጻሉ። ታድያ በነዚህ ፳ ዓመታት ውስጥ አስደሳችም አሳዛኝም ገጠመኝ እንዳላቸውም ይናገራሉ። እነዚህ ወጣቶች ክብረ በዓሉን ወደ ማስተናበር ሥራ ከመምጣታቸው በፊት ታቦቱን አጅበው ወደ ባሕረ ጥምቀቱ ሲሄዱ በነበረው መገፋፋት ወድቀው እግራቸውን እንደተጎዱና ሌላ ጊዜ ደግሞ ቦርሳቸውን መሰረቃቸውን ያስታውሳሉ።

ወ/ሮ አዜብ አክለውም ‹‹እነዚህ በጥምቀት በዓል በበጎ ፈቃድ የሚያገለግሉ ወጣቶች የማስተናነበር ሥራውን መሥራት ከጀመሩ ወዲህ ግን በዓሉ በሥነ ሥርዓት እንዲከበርና እንዲደምቅ ከማድረጋቸውም በላይ ታቦቱን አጅበው የሚሄዱት ካህናት የሚሄዱበትን መንገድ በማጽዳት፣ በማጠበና ጉዝጓዝ በመጎዝጎዝ እንዲሁም ምንጣፍ በማንጠፍ የክብረ በዓሉ ዋና አካል ሆነዋል። እነዚህ ወጣቶች ከአልባሌ ሥፍራ ርቀው ሕዝበ ክርስቲያኑ ታቦቱን አጅቦ ያለ መዋከብና መገፋፋት እንዲያከብር ሥርዓት ማስከበራቸው እጅግ የሚያስደስት ነው፡ ፡›› ሲሉ ይገልጻሉ።

ወጣት ዘካርያስ ጸጋዬም ወጣቶቹ የጥምቀት በዓልን ጨምሮ በየክብረ በዓላቱ ምእመናንን ለማገልገል የሚያሳዩት ትጋት እንደሚያስደስተው በመግለጽ ‹‹ወጣቶቹ ለጥምቀት በዓል ከከተራው ጀምሮ ክብረ በዓሉ እስኪጠናቀቅ ድረስ መንገድን በመጥረግ የተጠረገውንም መንገድ ጉዝጓዝ በመጎዝጎዝና ምንጣፍ በማንጠፍ እንዲሁም በሕዝበ ክርስቲያኑ መካከል መጨናነቅ እንዳይፈጠር በማስተናበር ያለ ድካም የሚሰጡት አገልግሎት የሚያስደንቅ ነው።›› ብሏል።

ከዚህ በተጨማሪም ‹‹የወጣቶቹ ትጋትና መንፈሳዊነት በክብረ በዓላቱ ሰሞን በቻ መሆኑ ግን ቤተ ክርስቲያንና መምህራን ያልሠሩት የቤት ሥራ እንዳለ ያሳያልና ወጣቶቹ በክብረ በዓላቱ ላይ የሚያሳዩት መንፈሳዊነት ዘላቂ እንዲሆንና የሚታዩባቸውን የሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን ጉለቶች እንዲያርሙ በማይቋረጡ የቤተ ክርስቲያን ትምህርቶች ሊታገዙ ይገባል›› ሲል አስገንዝቧል።

በመጨረሻም ‹‹ ቅድስት ቤተ ክርስቲያንም በየጊዜው ለሚገጥማት ፈተና እንደ ወጣቶቹ ተደራጅቶ የመጣ ኃይል ያስፈልጋታልና ወጣቶቹን ለክብረ በዓላት ጊዜ ብቻ ጠርቶ ከመገልገል ባለፈ ባሏት የአገልግሎት መዋቀሮች በማቀፍ በዘላቂነት ልትገለገልባቸው ይገባል። ለእነዚህ ወጣቶች ዛሬ ሥርዓት ሠርተን በቤተ ክርስቲያን መዋቀር ውስጥ ካላቀፍናቸው ነገ ለቤተ ክርስቲያን ችግር እንዳይሆኑ ሥጋት አለኝ›› ሲል ወጣት ዘካርያስ ሐሳቡን ያጠቃልላል።

# “መምህራኑ በሱስንዮስ ዘመን የከሸፈውን የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያን ካቶሊክ የማድረግ ተልዕኮ ወስደው የመጡ ነበሩ”

አቶ ከፈለኝ ኀይሉ

ካሳሁን ለምለሙ

ክፍል አንድ

*የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በጥንቃቄ የተሠራ ሥርዓት ባለቤት ናት። የአገልግሎት ተቋማቷ ሁሉ በሥርዓትና በመመሪያ የሚተዳደሩ ናቸው። ሥርዓትና መመሪያዎቹ ለሀገርና ለምእመናን ፍጹም ጠቃሚዎች ናቸው። በሥርዓትና በመመሪያ ከሚመሩ ተቋማት መካከል ደግሞ ሰንበት ትምህርት ቤቶች ናቸው። በኢትዮጵያ የሰንበት ትምህርት ቤቶች መሥረታ ታሪክ ቀላል ጊዜ ያለው አይደለም። ሰንበት ትምህርት ቤቶች በተለይ ወጣቱን ትውልድ በመንፈሳዊና በሥጋዊ ሕይወቱ ሙሉ ሆኖ እንዲያድግ የበኩላቸውን ድርሻ እየተወጡ ይገኛሉ። በሰንበት ትምህርት ቤቶች ምሥረታ ላይ በግንባር ቀደምነት የሚጠቀሰው የምስካየ ኅዙናን መድኃኔዓለም ገዳም ተምህሮ ማስተማር ሰንበት ትምህርት ቤት ነው።*



*አቶ ከፈለኝ ኃይሉ በምስካዬ ኅዙናን መድኃኔ ዓለም ገዳም ተምሮ ማስተማር ሰንበት ትቤት የሥራ አመራር ቦርድ አባል*

*ይህ ሰንበት ትምህርት ቤት በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሰንበት ትምህርት ቤቶች ምሥረታ ታሪክ የመጀመሪያው ነው። ሰንበት ትምህርት ቤቱ በተፈሪ መኮንን አዳሪ ትምህርት ቤት ይማሩ የነበሩ ጥቂት ኦርቶዶክሳውያን ወጣቶች የመሠረቱት ሲሆን ዓላማውም በተፈሪ መኮንን አዳሪ ትምህርት ቤት ውስጥ በመምህርነት ሞያ ተሠማርተው የሚገኙ ከካናዳ የመጡ ካቶሊካውያን በቤተ ክርስቲያንና በምእመናን ላይ ይፈጽሙት የነበረውን ሃይማኖታዊ ቅሰጣ ለመከላከል ነበረ። በሂደቱም ብዙ ውጣ ውረድን አልፈው ዓላማቸውን አሳክተዋል። ስለሆነም በጉዳዩ ዙሪያ የምስካየ ኅዙናን መድኃኔዓለም ገዳም ተምህሮ ማስተማር ሰንበት ትምህርት ቤት የሥራ አመራር ቦርድ አባል ከሆኑት አቶ ከፈለኝ ኃይሉ ጋር በሰንበት ትምህርት ቤቱ አመሠራረት፣ እንዲሁም የአገልግሎት ሂደት በተመለከተ አጭር ቆይታ አድርገናል። መልካም ንባብ።*

**ስምዐ ጽድቅ፡- የምስካየ ኅዙናን መድኃኔዓለም ገዳም ተምህሮ ማስተማር ሰንበት ትምህርት ቤት መቼ እና እንዴት ተመሠረተ?**

**አቶ ከፈለኝ ኃይሉ፡-** የመስካየ ኅዙናን መድኃኔዓለም ገዳም ተምሮ ማስተማር ሰንበት ትምህርት ቤት አመሠራረት የራሱ የሆነ ታሪካዊ ሂደት ያለው ሲሆን ይኸውም በ፲፱፻፴፰ ዓ.ም የራስ ተፈሪ መኮንን አዳሪ ትምህርት ቤት መቋቋሙን ተከትሎ የተመሠረተ ነው። ትምህርት ቤቱ ከተቋቋመ በኋላ በርካታ ተማሪዎችን ያስተምሩ የነበሩት ከካናዳ የመጡ ካቶሊካውያን ሚሲዮናውያ መምህራን ነበሩ። እነዚህ መምህራን በሱስንዮስ ዘመን የከሸፈውን የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያንና ምእመኖቿን ካቶሊክ የማድረግ ተልዕኮ ወስደው የመጡ ነበሩ። በወቅቱ ተልዕኳቸውን የጀመሩት ኢትዮጵያን ያስተዳድሩ ከነበሩት ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኀይለ ሥላሴ ሳይሆን ከኦርቶዶክሳውያን ተማሪዎች ወይም ከተራው ምእመናን ነበር። በዚህ መሠረት ካቶሊካውያኑ መምህራን የሚያስተምሯቸውን ተማሪዎች ካቶሊክ ለማድረግ ሥራ እየሠሩ መሆኑን የሚገልፅ ሪፖርት በፈረንሳይኛ አዘጋጅተው ወደ ካናዳ ለመላክ በዝግጅት ላይ እንዳሉ በወቅቱ ተማሪ የነበሩት ክቡር ደጃዝማች ወልደ ሰማያት ገ/ወልድ ተመለከቱት። በተመለከቱበት ወቅትም በጣም ይበሳጫሉ፤ በጣም ይጨነቃሉ።

በወቅቱ በድርጊቱ በጣም ስለአዘነም ከዚህ ቀደም ሱስንዮስ በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ላይ ሞክሮ ያልተሳካለትና የተሳካለት ነገር ምን እንደነበር ለማወቅ ጥረት አደረጉ። ወዲያውኑ ወደ ፒያሳ አካባቢ በመሄድ ስለሱስንዮስ የተጻፈ መጽሐፍ መመልከት ጀመሩ። በሂደቱም ካቶሊካውያን በዘመኑ በቤተ ክርስቲያን ላይ ያደርጉት የነበረውን ቅሰጣ ይረዳሉ። ይህንን ከተረዱ በኋላ ደጃዝማች ወልደ ሰማያት የተወሰኑ ተማሪ ጓደኞቻቸውን አስተባብረው “ካቶሊካውያኑ መምህራን ታሪካችንን እያንቋሸሹ ነው” በሚል ሰበብ እንዳያስተምሯቸው ተቃውሞ ማሰማት ጀመሩ። ተቃውሞውን ባሰሙበት ወቅት የተቃውሞው አነሳሽ ደጃዝማች ወልደሰማያት እንደሆኑ ስለደረሰበት

በትምህርት ቤቱ አስተዳዳሪ አማካይነት ከትምህርት ገበታቸው እንዲባረሩ ተደረገ። ከእርሳቸው መባረር በኂላ ግን ዐሥራ ሁለት በሚሆኑ ተማሪዎች ማኅበሩ እንደገና ተደራጀ። በወቅቱ ምስካየ ኅዙናን መድኃኔዓለም ገዳም ባለመኖሩ መሰባሰቢያቸውን ቅድስት ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን ያደርጉ ነበር። እዚያ በነበሩበት ወቅት ማኅበሩን በምሥጢር መሠረቱ።

የማኅበሩ ዓላማ የካቶሊክ ሚሲዮናውያን በቤተ ክርስቲያን ላይ የሚያደርጉትን ቅሰጣ መከላከል ሲሆን የማኅበራችን ዓላማ ብለው ለትምህርት ቤቱ ያሳወቁት ደግሞ ‹‹የተጣሉትን ለማስታረቅና የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት›› የሚል ነበር። ይህንን ማኅበር በመመሥረታቸውና በሚሲዮናውያኑ ላይ ክትትል በማድረጋቸው ደጃዝማች ወልደ ሰማያትን ጨምሮ ሌሎች ጓደኞቻቸው ከፍተኛ ዋጋ ከፍለዋል። ተማሪዎቹን እስከ ዩኒቨርስቲ ድረስ እየተከታተሉ ዋጋ ያስከፍሏቸው የነበሩት ደግሞ የተፈሪ መኮንን ትምህርት ቤት ርዕሰ መምህር የነበሩት ካናዳዊ ሚሲዮናውያንና የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የካቶሊክ ሚሲዮናውያን መምህራን ነበሩ። የተወሰነ ዋጋ ቢከፈልም ማኅበሩ በቅብብሎሽ ዓላማውን ሲያሳካ ቆይቷል። ከዚህ ቀደም እንደተገለጠው የማኅበሩ ዓላማ የካቶሊካውያኑን ቅሰጣ መከላከል ነበር። በወቅቱም ዓላማውን ያሳካ እንቅስቃሴ ተደርጓል።

**ስምዐ ጽድቅ፡- በወቅቱ በሀገራችን ሃይማኖታዊ ሥርዓተ መንግሥት እንደነበር ይታወቃል፤ ታዲያ ለምን ማኅበሩን በመሠረቱ ኦርቶዶክሳውያን ተማሪዎች ላይ ግፍ ተፈጸመ?**

**አቶ ከፈለኝ፡-** በወቅቱ የሀገራችን ኢትዮጵያ መሪ የነበሩት ቀዳማዊ ኀይለ ሥላሴ ስለነበሩ ንጉሡም ለቤተ ክርስቲያን ቀና አመለካከት የነበራቸውና በርካታ አብያተ ክርስቲያናት እንዲተከሉና አገልግሎቱ እንዲሰፋ ጥረት ያደረጉ ናቸው። ነገር ግን በዘመኑ ካቶሊካውያን መምህራኑን በብዙ ውጣ ውረድ ያመጧቸው በመሆኑ ተማረው ሥራቸውን አቋርጠው ወደ ሀገራቸው ተመልሰው እንዳይሄዱ ስጋት ስላደረባቸው በዝምታ ያልፏቸው ነበር። ንጉሡ ለትምህርት ባላቸው ቀና አመለካከት በመምህራኑ ምክንያት ትምህርት እንዲቋረጥ አይፈልጉም። ካቶሊካውያኑ ደግሞ በንጉሡ መፈለጋቸውን እንደጥሩ አጋጣሚ በመጠቀም በሱስንዮስ ዘመነ የነበረውን ስሕተት አርመው ቀስ በቀስ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያንን ካቶሊክ የማድረግ እንቅስቃሴ ያደርጉ ነበር። ከዚህ ቀደም በጻፉት ሪፖርትም ቤተ ክርስቲያንን በአጭር ጊዜ ውስጥ እንዴት ካቶሊክ ማድረግ እንዳለባቸው በግልፅ አስቀምጠውታል። ከውጭ የሚመጣው ርዳታ እንዳይቀርና በመከራ የመጡት መምህራን ተማረው ወደ ሀገራቸው እንዳይመለሱም በመፍራት ጉዳዩ በጥልቀት ለንጉሡ አልተነገራቸውም ነበር።

ይህ ሁሉ ታልፎ እንደገና በዐሥራ ሁለት ሰዎች ማኅበሩ ተመሠረተ። በትምህርት ቤቱ ጥላ ሥር የተመሠረተው ማኅበር የመጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር በሚል ነበር። በወቅቱ ዛፍ ሥር ተሰባስበው እየተማማሩ እያለ ምስካየ ኅዙናን መድኃኔዓለም ገዳም እዚያው ትምህርት ቤት ውስጥ እንዲሠራ አደረጉ። ከዚያም በየካቲት ሆስፒታል ውስጥ ቤተሳይዳ በሚባል ሥፍራ የነበረው ጸላት መጥቶ ገዳሙ ውስጥ ገባ። ገዳሙም የተመሠረተው ፲፱፻፵፪ዓ.ም ነው። ከዚያም ጊዜ ጀምሮ በገብረ ጊዮርጊስ አጋዥ በሚባሉ ሰው አማካይነት ማኅበሩ ተምሮ ማስተማር የሚል ስያሜ አግኝቷል።

**ስምዐ ጽድቅ፡- በዐሥራ ሁለቱ የቤተ ክርስቲያን ልጆች የተመሠረተው ማኅበር ለምን በምሥጢር ሆነ?**

**አቶ ከፈለኝ፡-** ተማሪዎቹ በወቅቱ የተሰባሰቡት በራስ ተፈሪ መኮንን አዳሪ ትምህርት ቤት ውስጥ የሚሠሩ ካቶሊካውያን መምህራን በቤተ ክርስቲያን ላይ የሚያደርሱትን ቅሰጣ ለመከላከል ነው፤ ከፍተኛ ተቃውሚቸውም በወቅቱ ከነበሩት የካቶሊክ መምህራን ጋር ነው፤ በትምህርት ቤቱ ያስተምሩ የነበሩ ካቶሊካውያን መምህራን ዓላማ ደግሞ ሙሉ ኢትዮጵያን ካቶሊክ ማድረግ ነው፤ ሀገራችን ከካናዳ መንግሥት ጋር ላለመቀያየምና የሚመጡ ርዳታዎች እንዳይቀሩ እንዲሁም መምህራኑ ተማረው ወደ ሀገራቸው ቢመለሱ መደበኛ ትምህርቱ እንዳይቋረጥ በማሰብ ንጉሡ ሳያውቁ ማኅበሩ በኅቡዕ እንዲቋቋም አድርጎታል። ይህም የሆነው በወቅቱ በቀጥታ መቃወም ስለማይቻልና መምህራኑንም ማስቀየም አስፈላጊ ሆኖ ባለመገኘቱ ነው። ማኅበሩ በነበረው እንቅስቃሴ ሥጋት ያደረባቸው አንዳንድ አባቶችም የማኅበሩ አባላት በትምህርት ቤቱ እንደ መደበኛ ትምህርት ይሰጥ የነበረውን የግብረገብ ትምህርት እንዲከታተሉ አድርገዋል።

**ስምዐ ጽድቅ፡- የካቶሊካውያኑ የቅሰጣ ዘዴ ምን ይመስል ነበር?**

**አቶ ከፈለኝ፡-** ካቶሊካውያኑ የቅሰጣ እቅዳቸውን በየጊዜው ወደካናዳ ይልካሉ። አለቆቻቸውም ለተመለከቱት ዕቅድ ግብረ መልስ ይልኩላቸው ነበር። እቅዶቻቸው የማኅበሩ መሪ አንዱ በነበሩት ክቡር ደጃዝማች ወልደ ሰማያት

እጅ በገባበት ወቅት ሁሉንም ተረድተውታል:: የእቅዱ መነሻም በሱስንዮስ ዘመን ከንጉሡ ጀምሮ ሕዝቡን ካቶሊክ ማድረግ የነበረ ሲሆን ያ ዘዴ ብዙም አዋጭ ያለመሆኑን ተረድተው ከንጉሡ ሳይሆን ከተራው ምእመን መጀመር አዋጭ መሆኑን የሚያነሳ ነበር:: የመጀመሪያው ርምጃ ተማሪዎችን ካቶሊክ በማድረግ ትምህርታቸውን ጨርሰው በየመሥሪያ ቤቱ በሚመደቡበት ወቅት የተቀረውን ሕዝብ ካቶሊክ የማድረግ አቅም ይኖራቸዋል ብለው ያምኑ ነበር:: ሕዝቡን ካቶሊካዊ ካደረግን በኋላ ንጉሡን ለመቀየር ቀላል እንደሆነ በየጊዜው ካናዳ ለሚገኙት አለቆቻቸው ያሳውቋቸው ነበር:: የማኅበሩ መሥራቾችና አባላት ቀድመው ጉዳዩን በመረዳታቸው የካቶሊካውያኑ ዕቅድ እንዳይሰምር በኅቡዕ ተደራጅተው ከፍተኛ ትግል አካሂደዋል::




*በምስካዬ ኅዙናን መድኃኔ ዓለም ገዳም ተምሮ ማስተማር ሰንበት ትቤት*

**ስምዐ ጽድቅ፡- ማኅበሩ ከተመሠረተ ጊዜ ጀምሮ የንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኀይለ ሥላሴ ድጋፍና ክትትል ምን ይመስል ነበር?**

**አቶ ከፈለኝ፡-** ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኀይለ ሥላሴ ለማኅበሩ ያበረከቱት አስተዋፅኦ በጣም ከፍተኛ ነበር:: ለማኅበሩ ያደረጉት ከነበረው ክትትልና ድጋፍ ባሻገር የማኅበሩ የበላይ ጠባቂ ሆነው አገልግለዋል:: ለቀለምና ለመንፈሳዊ ትምህርት ያላቸው አመለካከት ቀና በመሆኑ ማኅበሩን በየጊዜው ይጎበኛሉ፣ ይደግፋሉ፣ አመራሩንም ይከታተላሉ፤ እንዲሁም አጠቃላይ ዓመታዊ ጉባኤ ላይ ይገኙም ነበር:: የወቅቱ የማኅበሩ ፕሬዚዳንት ከነበሩት ክቡር አቶ አበበ ከበደ ጋር ንጉሡ ቀጥተኛ ትውውቅና ቀረቤታ ስለበራቸው ማኅበሩን ባገኙት አጋጣሚ ሁሉ ለመርዳት እጅግ የቀና ፍላጐት ነበራቸው:: ንጉሡ ይህንን ሁሉ ያደርጉት የነበረው ተማሪዎች በመንፈሳዊና በሥጋዊ ዕውቀት የበለጸጉ እንዲሆኑ ከመፈለጋቸው የመነጨ ነው:: የሰንበት ትምህርት ቤት በኢትዮጵያ ደረጃ የመጀመሪያ የሚባል ነው:: አንዳንዶቹ የቅድስት ሥላሴ ሰንበት ትምህርት ቤት ከምስካየ ኅዙናን መድኃኔዓለም ገዳም ሰንበት ትምህርት ቤት ማኅበር ተምሮ ማስተማር ይቀድማል ቢባልም መረጃዎች ግን ማኅበሩ እንደሚቀድም ነው መረጃ የሚያሳዩት:: የተምሮ ማስተማር ሰንበት ትምህርት ቤቱ በ፲፱፻፴፰ ዓ.ም የተመሠረተ ነው:: ተምሮ ማስተማር የሚለውን ስያሜ ያወጡት ገ/እግዚአብሔር አጋዥ የሚባሉ የማኅበሩ አካል ናቸው:: አባሉ ይህን ስያሜ ያውጡት እንጂ ያጸደቁትን ግን ንጉሠ ነገሥቱ ናቸው:: መምህር ላቀው አዲስ የተባሉ የማኅበሩ አባል ደግሞ የማኅበሩን ዓላማ ቀርጸዋል:: የማኅበሩ ዓላማ ሂዱና በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችሁ አሕዛብን ሁሉ አስተምሩ (ማቴ.፳፰፥፲፱) የሚለውን የጌታችንና የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ቃል በተግባር መተርጎም ነው:: ተምሮ ማስተማር ማኅበር ሰንበት ትምህርት ቤት ማኅበረ ቅዱሳንን ጨምሮ በርካታ ማኅበራትና ሌሎች ሰንበት ትምህርት ቤቶች እንዲመሠረቱ ምክንያት ሆኗል::

በተፈሪ መኮንን አዳሪ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ማኅበሩ መመሥረቱም የካቶሊካውያኑን ቅሰጣ ከመከላከል በተጨማሪ በትምህርት ቤቱ ውስጥ አባቶች ተመድበው ኦርቶዶክሳዊ ትምህርቶች እንዲሰጡ አግዟል:: ይህ ትምህርትም በሌሎች አካባቢዎች እንደ ግብረ ገብ ትምህርት ሲሰጥ ቆይቷል:: ይህ ውጤት የመጣው በተምህሮ ማስተማር ሰንበት ትምህርት ቤት ያልተቋረጠ ጥረት ነው:: ማኅበሩ እንደተጨማሪ ዓላማ ይዞ ሲንቀሳቀስ የነበረው የቤተ ክርስቲያንን ትምህርት በደንብ አውቆ ላላወቁት ማሳወቅ ሲሆን አባላቱም ሥርዓተ ጋብቻቸውን በተክሊልና በሥርዓተ ቁርባን እንዲፈጽሙ የማድረግ ሥራ እየሠራ ሲሆን ስብከተ ወንጌልንም በከፍተኛ ደረጃ አስፋፍቷል:: በርካታ የአማርኛ መዝሙሮችም የቤተ ክርስቲያንን ሥርዓትን ጠብቀው ለምእመናን እንዲደርሱ አድርጓል:: በርካታ የመጽሐፍ፣ የዜማና የግጥም ደራስያንንም አፍርቷል::

ማኅበሩ የመዝሙር መጻሕፍትም እንዲኖሩ አድርጓል፤ የዐደባባይ በዓላት ዛሬ የያዙትን መልክ ይዘው እንዲከበሩም ከፍተኛ ጥረት አድርጓል:: ጥምቀት በጃልሜዳ፣ የመስቀል በዓል ደግሞ በመስቀል አደባባይ በቋሚነት እንዲከበር የበኩሉን መሠረት የጣለ ማኅበር ነው:: ስብከትን ጨምሮ መንፈሳዊ ድራማዎችና ፊልሞች እንዲጀመሩ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያበረከተ ሲሆን የስድስት ኪሎ ዩኒቨርስቲ ተማሪዎች በተምሮ ማስተማር ሰንበት ትምህርት ቤት እንዲያልፉ ትልቅ ድርሻ ነበረው:: ንጉሡ በሥልጣን ላይ በነበሩበትና ከሥልጣን ከወረዱ በኋላም ቢሆን ማኅበሩ በተለይ ለወጣቶች በከፍተኛ ደረጃ የአርአያነት ሥራ ሲሠራ ቆይቷል::

# “ደግነት ለባቶቻችን የዕለት ተዕለት ተግባራቸው ቢሆንም በዚህ ክፉ ዘመን ያሳዩት ቆራጥነት ደግሞ በታሪክ ሲታወስ የሚኖር ነው”

ቀሲስ ይኽነው መልኩ

በዲ/ን አሻግሬ አምጤና በካሳሁን ለምለሙ

*በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል በተከሰተው ጦርነት ምክንያት ችግር ላይ ከወደቁት ቅዱሳት መካናት መካከል የደብረ ሮሃ ቅዱስ ላሊበላ ገዳም አንዱ ነው። አካባቢው የጦርነት አውድማ በነበረበት ወቅት የአካባቢው ማኅበረሰብ፣ አገልጋዮችና ቅርሱ ከፍተኛ የስጋት አደጋ ላይ ወድቀው እንደነበረ የቅርብ ጊዜ ትውስታ ነው። በወቅቱ የአካባቢው ማኅበረሰብ ብዙ ውጣ ውረድ ያሳለፉ ሲሆን በርካታ የመንግሥት አገልግሎት መስጫ ተቋማትና የግለሰብ ሀብት ንብረት ወድመዋል፤ተዘርፈዋል። በዚያ ክፉ ወቅትም የቤተ ክርስቲያናቸውንና የሕዝባቸውን አደራ ተቀብለው ኃላፊነታቸውን የተወጡ አንዳንድ ግለሰቦችም አሉ። የአካባቢው ምእመናን እንዳይራቡ፣ሀብት ንብረታቸው እንዳይዘረፍና ማኅበረሰቡ በሕክምናና በመድኃኒት እጦት እንዳይቸገሩ ብሎም እንዳይሞት የበኩላቸውን ሲያደርጉ ቆይተዋል። ከእነዚህ ግለሰቦች መካከል በደብረ ሮሃ ቅዱስ ላሊበላ የሚኖሩት ቀሲስ ይሄነው መልኩ (በአንድ ወቅት በቅዱስ ላሊበላ የሰበካ ጉባኤ አባል የነበሩና በአሁኑ ወቅት በመንግሥት ሥራ ተሠማርተው የሚገኙት) አንዱ ናቸው። ከእርሳቸው ጋር ያደረግነውን ቃለ መጠይቅ እንደሚከተለው አቅርበነዋል። መልካም ንባብ።*

**ስምዐ ጽድቅ፡- የላሊበላና አካባቢው ምእመናን በጦርነቱ ምክንያት ያሳለፉትን የመከራ ጊዜ ቢገልጹልን?**

**ቀሲስ ይኽነው መልኩ፡-** የጦርነት መልካም ነገር የለውም። ጦርነት በሰውና በንብረት ላይ ከፍተኛ ውድመት ያመጣል፤ በዚያ ምክንያት ረሀብ፣ ቸነፈር፣ ስደት፣ ድርቅና መሰል ተያያዥ ችግሮች ይከሰታሉ። በጦርነቱ ወቅት የደብረ ሮሃ ቅዱስ ላሊበላ ገዳምና የአካባቢው ማኅበረሰብ ከባድ ጊዜያትን አሳልፈናል። ወቅቱ ለቤተ ክርስቲያንና ለምእመናን ከባድ የፈተናና የጭንቅ ጊዜ ነበር። ምእመናን አካባቢያቸውን ጥለው ተሰደዋል። ማኅበራዊ አገልግሎት ይሰጡ የነበሩ የመንግሥት ተቋማት ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል ወድመዋል። በዚያ አስቸጋሪ ወቅትም በመልካም ዕሴት የሚኖረው ህዝባችባችን እርስ በእርሱ እየተረዳዳበትና ወንጀል እንዳይፈጸም የበኩሉን ድርሻ ሲወጣ የቆየበት ተግባር አንዱ ማሳያ ነው። ይህ በመሆኑም በዚህ ወቅት የታቀደውን ያህል ጉዳት በአካባቢው ሳይደርስ ቀርቷል።

ይህንን የመረዳዳትና የመተጋገዝ ዕሴት ከዚህ ቀደም በደንብ ተጠቅመንበትና አሳድገነው ቢሆን ኖሮ ለአካባቢው ብቻም ሳይሆን ለመላው ኢትዮጵያ ጠቃሚ ይሆን ነበር። ይህ ወቅት የሰውን ደግነትና አስተዋይነት በበቂ ሁኔታ ያየንበት ነው። ጦርነቱ በተጀመረ ጊዜ የአካባቢውን ደኅንነት ለመጠበቅ በአካባቢው ተሰማርተው የነበሩ ጥምር የጸጥታ ኃይሎች አካባቢውን ለቀው ከወጡ በኋላ አካባቢው በሕወሓት ታጣቂዎች ቊጥጥር ሥር በገባበት ወቅት ለቅርሱና ለቤተ ክርስቲያናችን ደኅንነት ስንል በተወሰኑ ሰዎች የመጣውን መከራ ሁሉ ለመቀበል በአካባቢያችን ተወስነን ቆይተናል። የተሰወሰኑ ሰዎችም አካባቢያቸውን ለቀው ወጥተዋል፣ ሌሎቹም በአካባቢው የቆየነው በከፍተኛ ፍርሃትና ጭንቀት


ቀሲስ ይኽነው መልኩ

ውስጥ ነበረ። ቢሆንም ግን የመጣውን መከራ ሁሉ እግዚአብሔር እንዲያስታግሥው ጥቂት ምእመናን ሆነን ጊዜውን በጸሎትና በምህላ ስናሳለፍ ቆይተናል። ምህላችንንና ጸሎታችንን ቸሩ እግዚአብሔር ተቀብሎት የመጣውን መከራ እንዳመጣጡ አስታግሦልናል።

ተቋማት ከዝርፊያና ውድመት እንዲጠበቁ፣ የተሰደደው ምእመን ወደ አካባቢው እንዲመለስ፣ እያንዳንዱ ምእመን ቤቱንና አካባቢውን ነቅቶ እንዲጠብቅ የቅዱስ ላሊበላ ገዳም ዋና አስተዳዳሪ ቆሞስ አባ ጽጌ ሥላሴ መዝገቡ ለምእመናን ባስተላለፉት መልእክት መሠረት ነገሮች መስተካከል ጀምረዋል።

በወቅቱ የተወሰኑ የአገልግሎት መስጫ ተቋማት ከጥቅም ውጭ በመሆናቸውና ኅብረተሰቡ እህል አስፈጭቶ የሚበላበት ወፍጮና ኃይል ባለመኖሩ ኅብረተሰቡ መቸገሩን የተመለከቱት ዋና አስተዳዳሪው ጀነሬተር ከተለያዩ ቦታዎች አስመጥተው ችግሩን በጊዜያዊነት ለመፍታት ሞክረዋል። በተጨማሪም አንዳንድ ከውድመት የተረፉ የግልም ሆኑ የመንግሥት ተቋማት እንዳይዘረፉ የጥበቃ አካላት በየቦታው እንዲስማሩ አድርገዋል። ደኖችም ጭምር እንዲጠበቁ በመደረጋቸው ማኅበረሰቡም በሰላም ወጥቶ በሰላም በመግባቱ በአካባቢው ከጊዜ ወደጊዜ ምቹ ሁኔታ እየፈጠረ መጣ። እኛም እንደልጅነታችን ከአባታችን ጋር ተባብረን የተለያዩ ሃይማኖታዊና ማኅበራዊ ተግባራትን ስንፈጽም ቆይተናል። በወቅቱ የነበሩት አደረጃጀቶች የቤተ ክርስቲያንና የእድር አደረጃጀቶች በመሆናቸው ባሉት አደረጃጀቶች ተጠቅመን ኅብረተሰቡን ለማገዝ ጥረት አድርገናል።

ይህም ቤተ ክርስቲያናችን የምእመናን አምባና መጠጊያ መሆኗን ያየንበት ወቅት ነበር። ተከታታይ የህክምና አገልግሎት ለሚፈልጉ የኅብረተሰብ ክፍሎችም ተገቢውን የሕክምና አገልግሎትና የመድኃኒት አቅርቦት እንዲያገኙ ጥረት ተደርጓል። የተቀናጀ የሕክምና አገልግሎት እንዲሰጥና ሀኪሞችንም የማረጋጋት ሥራ በመሥራት በሙያዊ አገልግሎታቸው ብቻ ትኩረት እንዲያደርጉ የማድረግ ሥራ ተሠርቷል። ሀኪሞች በወቅቱ ደመወዝ ሳይኖራቸው አገልግለዋል። ይሁን እንጂ ሀኪሞችን ጨምሮ የአካባቢው ምእመናን በረሀብ እንዳይጎዱ ቤተ ክርስቲያን የቻለችውን ሁሉ ስታደርግ ቆይታለች።

ይሁን እንጅ ሁሉም ነገር በእኛ አቅም ብቻ የሚሸፈን ስላልነበር አንዳንድ ነገሮችን የሚያግዘን አካል ያስፈልገን ነበር። በዚህ ሂደት ከአባታችን ጋር ተነጋግረን እኔ ወደ ባሕር ዳር ሄጀ መድኀኒት አመጣሁ። በተደጋጋሚ ከባሕር ዳር የመጣውት መድኀኒት ለብዙዎች በሕይወት የመቀጠል ምክንያት ሆነ። የመድኃኒትና የሕክምና ችግር ከሞላ ጎደል የተቀረፈላቸው ምእመናን በምግብ እጥረት ችግር ላይ እንዳይወድቁም ከበጎ አድራጊ ግለሰቦች ገንዘብ በመሰብሰብ ምእመናን የዕለት ጉርስ እንዲያገኙ ተደርጓል። ከዚያም አልፎ በተቋማት ጥበቃ ላይ ተሰማርተው ለሚገኙ አካላት ከተሰበሰበው ገንዘብ አከፋፍለናል። በአካባቢው ያሉ አብያተ ክርስቲያናት የተለመደ የዕለት ተዕለት አገልግሎታቸው እንዳይታጎል ከገዳማችን የዘቢብና የእጣን ድጋፍ አድርገናል። በአጠቃላይ መከራውን ለመቋቋም የተለያዩ ዘዴዎችን ተጠቅመን እዚህ ላይ ደርሰናል።

**ስምዐ ጽድቅ፡- በአስቸጋሪ ወቅት ራስን ለሕዝብና ለሀገር አሳልፎ መስጠት ስለሚያስገኘው ጥቅም ቢገልጹልን?**

**ቀሲስ ይሄነው፡-** ክርስትና በራሱ የመከራ ጉዞ መሆኑ ይታወቃል። በመከራ ዘመን ራስን ለሕዝብና ለሀገር አሳልፎመስጠት ያስፈልጋል።"ያለኝ ይበቃል"የሚለውን የወንጌል ቃልም በሕይወት መተግበር ያስፈልጋል። ይህንንም በወቅቱ በነበረው ችግር በተግባር ለመግለጥ ተሞክሯል። ‹‹ማንም ሰው በረሃብና በመድኃይኒት ማጣት መሞት የለበትም›› በሚል መሪ ቃል ሰዎች በረሀብና በሕክምና እጥረት እንዳይሞቱ ጥረት አድርገናል። እንደክርስቲያን መሪ ካህንና የበጎች እረኛ የሆነ ሰው በጎቹ እንዳይበተኑ፣እንዳይራቡና በችግር እንዳይሞቱ የማድረግ የሃይማኖትም ሆነ የሞራል ኃላፊነት አለበት። ከተቻለ ጦርነቱ እንዳይካሄድና በሰዎችና በንብረት ላይ ከፍተኛ ጉዳት እንዳያደርስ መሞከር፣ መገሰጽና ማውገዝ የካህናት ኃላፊነት ይሆን ነበር፤ ካልሆነ ደግሞ በጦርነቱ የከፋ ችግር እንዳይከሰት መከላከል ከተከሰተም በተቻለ መጠን የፈረሰውን መልሶ ለመጠገን መጣር፣ የተራበውን ማብላት፣ የተጠማውን ማጠጣት፣ የሞተውን መቅበር፣የታረዘውን ማልበስና የሕክምና እጦት ያለበትን ችግሩ እንዲወገድ መሥራትና ለችግሩ ደራሽ የሚሆን ወገኖችን ማነሣሣት የአባቶች ድርሻ ግንባር ቀደም መሆን አለበት።

ጦርነቱ በሀገርና በቤተ ክርስቲያን ላይ ከፍተኛ ውድመትና ውድቀት ተከስቷል። ውድመቱ ከደረሰም በኋላ ኦርቶዶክሳውያን አባቶች የተጎዱ ወገኖችን በቻሉት ሁሉ ሲደግፉ ቆይተዋል። ለዚህም የሰሜን ወሎ፣ የደቡብ ወሎና የኦሮሞ ብሔረሰብ አስተዳደር ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ብፁዕ አቡነ ኤርምያስ፣ የዋግኽምራ ሀገረ ስብከት ሊቀጳጳስ ብፁዕ አቡነ በርናባስና የደቡብ ወሎ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ብፁዕ አቡነ አትናቴዎስ የእውነተኛ አባትነት ምስክሮች ናቸው። አባትነትን በተግባር አሳይተዋልና። ደግነት የአባቶቻችን የዕለት ተዕለት ተግባራቸው ቢሆንም በዚህ ክፉ ዘመን ያሳዩት ቆራጥነት ደግሞ በታሪክ ሲታወስ የሚኖር ታላቅ ተግባር ነው። በዚያ ክፉ ጊዜ ምእመናን የሚያፅናናቸው ቤተ ክርስቲያን ደግሞ

የሚጠብቃት በሚፈልጉበት ወቅት አባቶቻችን ያሳዩት አባታዊ ተግባር ለትውልድ መልካምነትንና ከራስ በላይ ለሌሎች መኖርን የሚያሳይ ነው፡፡

**ስምዐ ጽድቅ፡- አንዳንድ የኅብረተሰብ ክፍሎች ለቤተ ክርስቲያን ያላቸውን የተሳሳተ አመለካከት ከማረም አንፃር እንደነዚህ ዓይነት መልካም ተግባራት ምን ዓይነት አስተዋጽኦ ይኖራቸዋል ብለው ያምናሉ?**

**ቀሲስ ይሄነው፡-** በሰዎችም ዘንድ ይሁን በሚዲያዎች በብዛት የሚነገረው ስለ ክፉ ነገር ወይም ስለ ፖለቲካ ጉዳይ ነው፡፡ በቅርብ ጊዜ ብቻ ካልሆነ በስተቀር ስለ አባቶቻችን ደግነት፣ አስታራቂነት፣ አስተማሪነት፣ ደጋፊነት፣ የቁርጥ ቀን ዋስነት እንዲሁም አሻጋሪነት ሲወራ ሰምተን አናውቅም፡፡ አባቶቻችንም መልካም ተግባራቸውን እግዚአብሔር እንዲቀበልላቸው እንጂ የሰው ልጅ ሰምቶ አውቆላቸው እውቀና ወይም ሽልማት እንዲሰጣቸው አይሹም፡፡

የአባቶቻችን መልካም ተግባርም በጊዜ ሂደት እየተገለጠና ሥራቸው ምስክር እየሆነ የሚመጣ እንጂ በሚዲያ ወይም በሰው አንደበት የሚነገር ወይም የሚወደስ አይደለም፡፡ በሌሎች ዘንድ ለአባቶቻችንና ለቤተ ክርስቲያናችን የሚሰጠው እይታም ከዚህ ቀደም የተዛባ ነበር፡፡ ይህ ማለት አባቶቻችንም ሆኑ ቤተ ክርስቲያናችን ለወገንና ለሕዝብ የሚጠቅም ሥራ ሳይሠሩ ቀርተው አይደለም፡፡ ነገር ግን አልተገለጠም፤ በጦርነት ወቅት አባቶቻችን ያደረጉት ተጋድሎ በሚዲያ መገለጡና በሕዝብ ዘንድ መታወቁ በአማንያንም ሆነ በኢ-አማንያን ለአባቶችም ሆነ ለቤተክርስቲያን ያለው በጎ ያልሆነ አመለካከት እንዲቀየር አድርጎታል፡፡ ሰላም ሲመጣ ነገሮች ሲስተካከሉ ትውልዱ የአባቶችንና የቤተ ክርስቲያንን ውለታ ሊረሳ ይችላል፡፡ ይህ ተግባር የተለመደ ነው፡፡ የቤተ ክርስቲያንንና የአባቶቻችንን ውለታ ወጣቱ ትውልድ በደንብ እንዲረዳ ተከታታይ የሆነ ቤተ ክርስቲያናዊና ሀገራዊ ጥረት ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ቤተ ክርስቲያንንና አባቶችን የሚሰማ ትውልድ መፈጠር መቻል አለበት፡፡ ከስሜታዊነት የጸዳ ውስጣዊ አክብሮትም መስጠት ተገቢ ነው፡፡

**ስምዐ ጽድቅ፡-እንደነዚህ ዓይነት ፈተናዎች የራሳችን የሆነ ነገርን እንድንጠቀም ምን ያስተምሩናል ይላሉ?**

**ቀሲስ ይሄነው፡-** ቻይናዎች የብረት ማንኪያ ይሠራሉ፤ ነገር ግን በማንኪያው አይመገቡም፡፡ ይልቁንም ባሕላቸውን የጠበቀ ከእንጨት የተሠራ መቆንጠጫ የመሰለ ማንኪያ ይጠቀማሉ፡፡ የእኛ ሕዝብም በደግም ሆነ በክፉ ዘመን በእጁ ፈጭቶ ይበላ የነበረው አሁን ያን ሁሉ ረስቶ በዘመናዊ ወፍጮ ማስፈጨትን መልመዱ ክፉ ወቅት ሲመጣ መቸገሩን እያየን ነው፡፡ ያሁኑ ትውልድ በእጅ ተፈጭቶ እንደሚበላ የማያውቅ ሆኗል፡፡ ይህም ለረሀብና ለከፋ ችግር አጋልጦታል፡፡ እናቶቻችንና አባቶቻችን ሰዓት፣ ጊዜና ወቅትን በፀሐይ ጥላና በዶሮ ጩኸት የሚለዩ ነበሩ፡፡ ያውም እንደዚህ ዘመን ዘመናዊ የእጅ ሰዓትና የእጅ ስልክ ባልነበረበት ወቅት ነው፡፡ በዚህ ዘመን መከራና ፈተናው በበዛበት ወቅት የአባቶቻችንን የቀደመ ብልሃት በመጠቀም ችግሮቻችን ማለፍ ያስፈልጋል፡፡ የምንንቃቸው አባቶቻችንና እናቶቻችን ይጠቀሙባቸው የነበሩ ዘዴዎችንና መገልገያዎችን “የእኔ ናቸው” ብለን መቀበል ብንችል መልካም ነው፡፡ የእኛ የሆነን ነገር ሁሉ መጣል ሀገርንና ቤተ ክርስቲያንን ዋጋ ያስከፍላል፡፡ ትውልዱ በቴክኖሎጂ ብቻ ጥገኛ ከመሆን ይላቀቅ፡፡

**ስምዐ ጽድቅ፡- በደብረ ሮሃ ቅዱስ ላሊበላ ገዳም በአገልግሎት ላይ ላሉና ቅርሳቸውን በትጋት ለሚጠብቁ በርካታ አገልጋዮች ቋሚ የገቢ ምንጭ እንዲኖራቸው ምን መደረግ አለበት ይላሉ?**

**ቀሲስ ይሄነው፡-** ይህ ጉዳይ ሁሉንም አገልጋዮች የሚያሳስብ ነው፡፡ እንደሚታወቀው ገዳሙ በአብዛኛው የሚተዳደረው ወይም ለአገልጋዮች የሚከፈለውን ወርኃዊ ክፍያ የሚያገኘው ከቱሪዝሙ ዘርፍ ነው፡፡ ከቅርብ ዓመታት ጀምሮ በሀገሪቱ በተከሰተው የሰላም ማጣትና ፖለቲካዊ አለመረጋጋት የተነሣ የቱሪስት ፍሰቱ ተቋርጧል፡፡ ይህም በገዳሙ ገቢ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ አስከትሏል፡፡ ከቱሪስት የሚገኘውን ገቢ ብቻ እየጠበቁ መኖር አዋጭ አካሄድ ባለመሆኑ ሌላ አማራጭ የገቢ ምንጭ መፍጠር ያስፈልጋል፡፡ አማራጭ የገቢ ምንጭ የሚሆን ፕሮጀክት በመንደፍ ተግባራዊ ማድረግ ያስፈልጋልም፡፡ ከቱሪዝሙ ዘርፍ ብቻ የምንጠብቀውን ገቢ የተለያዩ አምራች ፋብሪካዎችን በመትከል ለቤተ ክርስቲያንንም ሆነ ለወጣቱ የሥራ እድል መፍጠር ይቻላል፡፡ ምእመናን ገዳሙ የራሱ የሆነ ገቢ እንዲኖረው የበኩላቸውን አስተዋጽኦ እንዲያበረክቱ ያስፈልጋል፡፡ ገዳሙ ዓለም አቀፍ ቅርስ በመሆኑ ለሀገርና ለቤተ ክርስቲያን እያበረከተ ያለውን አስተዋጽኦ ከግምት ውስጥ በማስገባት ገዳሙን እያገለገሉ ላሉ አገልጋዮች ቋሚ የሆነ የገቢ ምንጭ እንዲፈጠርላቸው የሁሉም ድርሻ ሊሆን ይገባል፡፡ ቤተ ክርስቲያንም በርካታ ምሁራን የተሳተፉበት ፕሮጀክት ነድፋ ተግባራዊ ብታደርግና ገዳሙና አገልጋዮች ተጠቃሚ ቢሆኑ መልካም ነው፡፡

# የጥምቀት በዓል አከባበር

ምኒልክ ብርሃኑ

ልጆች! እንደምን አላችሁ የአምላካችን የእግዚአብሔር ስም የተመሰገነ ይሁን በጣም ደኅና ነን፡፡ በባለፈው ቆይታችን ስለ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የልደት በዓል አከባበር ተምረናል፡፡ እናንተም በተማርነው መሠረት የጌታችንን ልደት በፍጹም ደስታ እና ሐሴት እንዳከበራችሁ እናምናለን፡፡ በዛሬ ቆይታችን ደግሞ ከገና ልደት በኋላ ስለምናከብረው የጥምቀት በዓል እንነግራችኋለን፡፡

ልጆች! የጥምቀት በዓል እናንተ አካባቢ እንዴት ነው የሚከበረው? አዎ ልጆች! የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ የጥምቀት በዓል በተለያዩ አካባቢዎች በደመቀ መልኩ ይከበራል፡፡ በዓሉን የምናከብረው ደግሞ ከጥር ዐሥር ጀምረን ነው፡፡ ታዲያ ልጆች! በዚህ ቀን እኛ ክርስቲያኖች ነጭ የሀገር ልብስ ለብሰን፣ አምረን እና ተውበን ቅዱሱን ታቦት አጅበን ከሰንበት ተማሪዎች ጋር እየዘመርን፣ እልል እያልን ወደ ጥምቀት ባሕር ወይም ታቦታቱ ወደ ሚያድሩበት ቦታ እንሔዳለን፡፡



*በጥምቀተ ባሕር ሕፃናት ሲጠመቁ*

ከዚያም በነጋታው ጥር ፲፩ ከመቼውም ጊዜ በበለጠ የሚያምር ልብስ ለብሰን፣ አዲስ ጫማ ተጫምተን በጠዋት ታቦቱ ካደረበት ሥፍራ እንገኛን፡፡ በሥፍራው ካህናት አባቶች የተሰበሰቡትን ክርስቲያኖች በጠበል እየረጨ ያጠምቋቸዋል፡፡ እኛም ከተጠመቅን በኋላ የእግዚአብሔር ማደሪያ የሆነው ቅዱስ ታቦቱን በካህናቱ ዝማሬ በምእመናን እልልታ በሆታ ታጅቦ ወደ ቤተ ክርስቲያን ይመለሳል፡፡ በዚህ ጊዜ ሁሉም ክርስቲያ ከቤቱ በመውጣት ቅዱስ ታቦቱን ይሸኛል ማለት ነው፡፡

ታዲያ ልጆች! በዚህ መልኩ የምናከብረው የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ የጥምቀት በዓል ትልቅ ሃይማኖታዊ አስተምህሮ አለው፡፡ እስኪ እኛ ክርስቲያኖች የጥምቀት በዓል ለምን እንደምናከብር ለጓደኞቻችሁ ንገሩዋቸው፡፡

ልጆች! መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚያስተምረን በገዳም ውስጥ ለሠላሳ ዓመት ለብቻው እግዚአብሔርን እያመሰገነ የሚኖር አገልጋይ ነበር፡፡ ይህ የእግዚአብሔር አገልጋይ ስሙ ቅዱስ ዮሐንስ ይባላል፡፡ ልጆች! የቅዱስ ዮሐንስ በምድር ላይ ሲኖር ይለብስ የነበረው የግመል ቆዳ ነበር፤ የሚበላው ደግሞ በበረሃ የሚገኝ ማር ነው፡፡ ታዲያ በዚህ በገዳም ውስጥ ሲኖር ሁል ጊዜ እግዚአብሔርን በደስታ እየዘመረ ያመሰግነው ነበር፡፡

ከዕለታት ባአንድ ቀን ከሚኖርበት ገዳም ተነሥቶ ዮርዳኖስ ወደሚባል ወንዝ እያስተማረ መጣ፡፡ የሚስተምረው ትምህርት ደግሞ "መንግሥተ ሰማያት ቀርባለችና ንስሐ ግቡ" የሚል ነበር፡፡ በዚህ ጊዜ በዮርዳኖስ ወንዝ አካባቢ የሚኖሩ ሰዎች ወደ እርሱ ይመጡ ነበር፡፡በትምህርቱም አምነው ያጠፉትን ጥፋት፣ የበደሉትን በደል እና የሠሩትን ኃጢአት ሁሉ ይነግሩት ጀመር፡፡ ቅዱስ ዮሐንስም ንስሓቸውን እየተቀበለ በዮርዳኖስ ወንዝ አጠመቃቸው፡፡ (ማቴ. ፫÷፩–፮)

በዚህ ጊዜ ፈጣሪያችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ዮርዳኖስ ወንዝ ሊጠመቅ መጣ። ቅዱስ ዮሐንስ ኢየሱስ ክርስቶስን ሲያየው ደነገጠ። ከዛም ወደ እርሱ ቀረበና "ፈጣሪዬ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ አጥምቀኝ" አለው። ኢየሱስ ክርስቶስ ግን "አይሆንም አንተ አጥምቀኝ" አለው። በኋላም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በቅዱስ ዮሐንስ እጅ በዮርዳኖስ ወንዝ ተጠመቀ። የተጠመቀበትም ቀን ጥር ፲፩ ነው።

ልጆች! ከዚያም ምን ሆነ መሰላችሁ? ኢየሱስ ክርስቶስ ተጠምቆ ከውኃው ሲወጣ በጣም የሚያስደንቅ ተአምር ታየ።

እርሱም ሰማያ ተከፈተ፤ ከዛም ከሰማዩ ውስጥ መንፈስ ቅዱስ በነጭ ርግብ ተመስሎ መጣና በኢየሱስ ክርስቶስ በራሱ ላይ ተቀመጠ። ከዚያም




*ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዮርዳኖስ ወንዝ ሲጠመቅ*

ከሰማይ ውስጥ "በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው" የሚል ታላቅ ድምፅ ተሰማ። በዚያ የተሰበሰቡትም ሕዝቡ ባዩት ነገር በጣም ተደነቁ።

ልጆች! ከዚህ ጊዜ በኋላ ዘወትር በየዓመቱ ጥር ፲፩ ቀን አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተጠመቀበትን ቀን በማሰብ እናከብራን ማለት ነው። ጌታችን የተጠመቀው ደግሞ በተወለደ በ፴ ዓመቱ ነው። በጥምቀት በዓል ጌታችን ወደ ዮርዳኖስ ሄዶ እንደተጠመቀ ለማስታወስ ጥር ፲ ቀን ሁሉም ታቦታት በአቅራቢያቸው ወደሚገኝ ውኃ ወዳለበት ስፍራ በመሔድ በድንኳን ውስጥ ያድራሉ። ይህ ዕለት ከተራ ይባላል።

ልጆች! ከተራ ማለት ከተረ ገደበ ካለው የግዕዝ ቃል የወጣ ነው። ከተራ የተባለው ደግሞ በአካባቢው ያለው ውኃ ተገድቦ ሕዝቡ እንዲጠመቅበት በዋዜማው ስለሚዘጋጅ ነው። ታቦታቱ ወደ ድንኳኑ ከገቡ በኋላ ሌሊቱን ካህናቱ ሲያመሰግኑ፣ ሲዘምሩና ሲቀድሱ እና ዕለቱን የተመለከተ ትምህርት ለሕዝቡ ሲያስተምሩ ያድራሉ። ጠዋት ከ፲፪ ሰዓት ጀምሮ በተጠራቀመው ውኃ አጠገብ ጸሎት ከተደረገ እና ከተባረከ በኋላ ለተሰበሰበው ምእመናን ይረጫል። ካህናቱ ሕዝቡን ጸበል ከረጩ በኋላ ልዩ ልዩ ሥርዓቶች ይደረጋሉ። ከዚያም ታቦታቱ ከድንኳን ወጥተው ወደየመጡበት ቤተ ክርስቲያን ይሔዳሉ።

ልጆች! አሁን ለምን የጥምቀትን በዓል እንደምናከብር በደንብ ተረዳችሁ አይደል፣ ጎበዞች! በሉ ለአሁኑ በዚህ ይብቃን። በሚቀጥለው በሌላ ታሪክ እስከምንገናኝ ድረስ ደኅና ሁኑ ልጆች።

ወስብሐት ለእግዚአብሔር

# ባለቤት ያጡት መጻሕፍት

**ኪኑኪሩ ከአዲስ አበባ**

ቤተ ክርስቲያን መጻሕፍትን የአገልግሎቷ መሣሪያ ማድረግ የጀመረችው መጻሕፍት ከተጻፉበት ጊዜ ጀምሮ ነው:: የብሉይ ኪዳን መጻሕፍትን አብራርቶ ተርጉሞ፣ ወንጌልን መስበክ ዋነኛ ተግባራቸው የነበሩ ሐዋርያትም ከመጻሕፍት የተለየ አገልግሎት አልነበራቸውም:: መጻሕፍትን፣ ያነባሉ፤ መልእክቶችን ይጽፋሉ:: በዚሁ መንገድ የመጻሕፍት አገልግሎት ዋና አስፈላጊም ትውፊታዊም የአገልግሎት አካል ሆኖ እናገኘዋለን:: ለዚህም ቅዱስ ጳውሎስ ለልጁ ለጢሞቴዎስ በጻፈው መልእክት ‹‹ስትመጣ በጢሮአዳ ከአክርጳ ዘንድ የተውሁትን በርኖሱንና መጻሕፍቱን ይልቁንም በብራና የተጻፉትን አምጣልኝ::›› (፪ኛ ጢሞ ፬÷፲፫) ያለው ቃሉ ለዚህ እንደ ማስረጃ ሊጠቀስ ይችላል::

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት ከጥንት ጀምሮ ብራና ፍቀው፣ ቀለም በጥብጠው ቅዱሳት መጻሕፍትን እየጻፉ ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ሲያውሉ እንደነበር ይታወቃል:: በተጨማሪም ሱርስት፣ ከግሪክ፣ ከዕብራይስጥና፣ ከአረብኛ ቋንቋ ወደ ግእዝ ቋንቋ ሲተረጉሙ ኖረዋል:: ከዚያም አልፈው ለትርጓሜ፣ ለምክር፣ ለተግሣጽ፣ ለውዳሴ፣ ለቅዳሴ፣ ለቤተ ክርስቲያን ሥርዓት ያስፈልጋል ያሉትንም ሁሉ እያደራጁ፣ የቤተ ክርስቲያንን ታሪክ፣ የቅዱሳንን ገድልና ድርሳን፣ እግዚአብሔር ያደረገውን ቅዱሳኑም በእግዚአብሔር ስም የሠሩትን ተምአራት ሁሉ ጽፈዋል:: ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን ብቻ ሳይሆኑ ነገሥታቱም፣ መኳንንቱም፣ መሳፍንቱም … ለቤተ ክርስቲያን ይጠቅማል ያሉትን ለራሳቸውም የሚያገለግሉ የጸሎትና የምስጋና መጻሕፍትን ያጽፉም፣ ያስተረጉሙም ነበር:: እነዚህ ከጥንት ጀምሮ በብራና የተጻፉ መጻሕፍትም ከትውልድ ትውልድ እየተወረሱ ከእኛ ዘመን ደርሰዋል::

አባቶቻችን በየዘመኑ በብዙ ድካምና ጥረት ያዘጋጇቸው መጻሕፍቱ ከዚህ የደረሱት ጉዳት ሳይደርስባቸው ለአደጋ ሳይጋለጡ ቀርተው አልነበረም:: በስርቆት፣ በቃጠሎ፣ በዝርፊያ ጠፍተው፣ በዓይነትም በቁጥርም አንሰው የቀሩት እኛ ዘመን ላይ ደርሰዋል:: እነዚህም መጻሕፍት በየአብያተ ክርስቲያት፣ በታላላቅ ገዳማትና አድባራት ዕቃ ቤቶች ውስጥ ተጠብቀው ኖረዋል:: የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በሀገሪቱ የኅትመት ቴክኖሎጂ ሲስፋፋ ከእነዚህን መጻሕፍት በወረቀት ኅትመት በርካቶቹን በማሳተም ለምእመናናን ስታቀርብ ቆይታለች::

በቤተ ክርስቲያን በግዕዝ ተጽፈው የነበሩትን ወደ አማርኛ ቋንቋ በመተርጎም አሳትሞ ለማሰራጨት ትንሣኤ ዘጉባኤ እና ተስፋ ገብረ ሥላሴ ማተሚያ ቤቶችን በመሰሉ የኅትመት ተቋማት ታትመው ሲሰራጩ ቆይተዋል:: በርካታ ምእመናንንም ለምክር፣ ለተግሣጽ፣ ለጸሎት፣ ለትምህርት፣ለምስጋና የሚያስፈልጓቸውን መጻሕፍት አግኝተው ለመጠቀም ችለዋል:: አብዛኞቹም መጻሕፍት በሊቃውንት ጉባኤ ታይተው መውጣታቸው እየተጠቀሰ የታተሙ በመሆናቸው የቤተ ክርስቲያን መሆናቸውን አምኖ ለመቀብል ብዙ አያስቸግርም ነበር::

ከጊዜ ጊዜ ግን ይህ ሁኔታ እየተለወጠ የቤተ ክርስቲያን መጻሕፍት ከቤተ ክርስቲያን መዋቅር ጋር ምንም ዓይነት ተቋማዊ ትስስር በሌላቸው ግለሰቦች እየታተሙ ሲወጡ ማየት እየተለመደ መጥቷል:: ድርሳናት፣ ገድላት፣ ቅዳሴያት፣ የጸሎት መጻሕፍት ወዘተ ሁሉ በግለሰቦች እየታተሙ በመሰራጨታቸው የግል ጥቅም መሰብሰቢያ ሆነዋል:: እነዚህ ግለሰቦቹም ካልዘሩበት የሚያጭዱ፣ ካልደከሙበት የሚሰበስቡ በመሆናቸው ወንጀል በሆነ ድርጊት ውስጥ ገብተዋል:: አንድን ቅዱስ ገድል የሚያሳትመው በቅዱሱ ስም የተቋቋመው አጥቢያው ወይም የሚመለከተው የቤተ ክህነቱ መዋቅር አካል የሆነ ተቋም መሆን ሲገባው ማንነቱ የማይታወቅ ግለሰብ ሲሆን እጅግ በርካታ ፈተናዎችን በቤተ ክርስቲያን ላይ የሚስከትል ነው:: በመጀመሪያ ቤተ ክርስቲያን ከኅትመት ሥራው

የሚገኘው ጥቅም ለአገልግሎቷ መልሳ ስለምታውለው የሚያስፈልጋትን ሀብት ታጣለች፡፡ መጻሕፍት ከሚያስገኙት ኢኮኖሚያዊ ጥቅም በላይ ግን አሳሳቢው በመጻሕፍቱ ይዘት ላይ ሊመጣ ለሚችል የትኛውም ዓይነት ለውጥ ላለመኖሩ ዋስትና አለመኖሩ ነው፡፡ መጻሕፍቱም ሲቆነጸሉ፣ ሥርዋጽ ሲገባባቸው ያልነበረ እንዳለ፣ የነበረው እንደሌለ ሊቀርብ ይችላል፡፡ ይህ ደግሞ ከሃይማኖት፣ ከሥርዓት አንጻር አሉታዊ ጥያቄ ያስከትላል፡፡

ሌላው ከዚህ ቀደም ሚሲዮናውያን ግእዝ ቋንቋ አጥንተው፣ የቤተ ክርስቲያንን የሥነ ጽሑፍ ባህል ዐውቀው መጻሕፍቷን ለመበረዝ፣ ለመከለስ ያደርጉ በነበረው ጥረት የአሁናቹ አሳታሚዎችስ በዚህ ጎዳና እንደማይጓዙ መተማመኛ ይኖራልን? አሁንስ በዘመናችን ያሉ መናፍቃንና አፅራረ ቤተ ክርስቲያን ይሄንን ክፍተት ሊጠቀሙበት አይችሉምን? በተለይ ምእመናንን በስፋት በሚጠቀሙባቸው የጸሎት መጻሕፍት፣ በገድላትና ድርሳናት ውስጥ ሊፈጸም የሚችል ማሳሳቻ ይዘት አሳሳቢ ነው፡፡ ከይዘት ባሻገርም ለቅዱሳት መጻሕፍቱ ክብር በማይመጥን የኅትመት ዓይነትና ደረጃ ለጉዳት በቀላሉ ሲጋለጡ፣ በዲዛይንና በኅትመት ጥራት የወረዱ፣ የጠራ የአርትዖት ሥራ ያልተሠራላቸው ሆነው ሲቀርቡ ለቅዱሳት መጻሕፍት መጻሕፍት ይሰጡት የነበረ ክብር ይሸረሸርና አሽገው፣ ደጉሰው በማኀደር አኑረው የመጠቀም ባህል ያዳከማል መጻሕፍቱንም እንደ አልባሌ እንዲታዩ ሊያደርግ ይችላል፡፡

በዚህ ሁኔታ ጉዳት የሚያስከትል ነገር በግልጽ እየታየ ሕጋዊ በሆነ መንገድ አሠራሩን ሥርዐት ለማስያዝና ግለሰቦቹን ለማስቆም ጥረት ማድረግ የነበረበት የቤተ ክህነቱ አካል እንቅስቃሴ አለማድረጉ በእጅጉ አስተዛዛቢ ነው፡፡ ቢቻል በሊቃውንት ጉባኤ በየጊዜው እየተመረመሩ ኅትመቶች በስፋትና በተመጣጣኝ ዋጋ መቅረብ ነበረባቸው፡፡ ይህ ባለመሆኑ ምእመናን እየታዘቡ ሳለ የቤተ ክርስቲያን መጻሕፍት በግለሰቦች እንደተፈለገ እየተቆነጸጸሉ፣ እየተሸነሸኑ፣ እየተደበሉ ታትመው ለገበያ ሲወጡ ‹‹ተዉ!›› ባለቤት የሚል መጥፋቱ በእጅጉ አሳሳቢ ሆኗል፡፡ ይህ በዚህ ከቀጠለ ግን ከዓመታት በኋላ የመጻሕፍቱ ዓይነትና ይዞታ የተዘበራረቀ ሆኖ ምእመናን ግራ የሚጋቡበት፣ ትውልዱም የሚደናገርበት እንደሚሆን መገመት ቀላል ነው፡፡

በተለይ አሁን ትውልዱ ቤተ ክርስቲያኑን ለማወቅ ፍላጎት ባሳየበት በዚህ ዘመን፣ በቤተ ክርስቲያን ያሉትን የጽሑፍ ሀብቶችም ሁሉ የመመርመር ጉጉት ባደረበት በዚህ ጊዜ ቤተ ክህነት አስፈላጊ የሚላቸውን መጻሕፍት እየለየ በየጊዜው ማሳተም ባልቻለ ቁጥር የምእመናንን ፍላጎት ለራሳቸው ጥቅም ለማዋል የሚሹ ግለሰቦችና ቡድኖች ቁጥር እንደሚጨምር ማሰብ ያስፈልጋል፡፡ እነዚህ ግለሰቦች በየዕቃቤቶቻችን ያሉ መጻሕፍትን፣ በሙዚየምና በታላላቅ አብያተ መጻሕፍት መደርደሪያዎች ላይ ያሉ የቤተ ክርስቲያን መጻሕፍትን ሁሉ በፈለጉት መጠንና ዓይነት ያለማንም ተቆጣጣሪና ገምጋሚ ማሳተማቸውን ሊቀጥሉ እንደሚችሉ አያጠራጥርም፡፡

ምእመናን በማያቋርጥ ሁኔታ የጸሎት መጻሕፍትን ገድላትና፣ ድርሳናትንም ይፈልጋሉ፡፡ ነገር ግን በበቂ መቅረብ ባልቻሉ፣ ጥቂት የታተሙ ቅጂዎችን ቢኖሩም እንኳን በውድ ዋጋ ስለሚቀርቡ ምእመናንን ለመግዛት ሲቸገሩ አማራጭ ወደሚሉት መሄዳቸው አይቀሬ ነው፡፡ ስለዚህ ቤተ ክህነት አቅርቦትንም ለማስፋት የሚያስችል የኅትመትና የአሳታሚነት አቅሙን ማሳደግ ግድ ይለዋል፡፡ ለብዙ ዐሥርት ዓመታት አገልግሎት ሲሰጥ የቆየውን የትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያን አቅም አሁንም በበለጠ ማሳደግና ማስፋት፣የማሳተምና የኅትመት ተግባራትን በሥርዓቱ እንዲያከናውን ማበረታታት ያስፈልገዋል፡፡ በአጠቃላይ ሲታይም የቤተ ክርስቲያን መጻሕፍት ባለቤት አልባ የሆኑ ይመስላልና፡፡ ቤተ ክርስቲያን የእኔ ናቸው የምትላቸውን ሀብቶቿን መጠበቅ አለባት፡፡ ይሄንን የማድረግ ኃላፊነት የሚጠበቅበት ቤተ ክህነት በዚህ ረገድ እንደዘመኑ መዘመን ይገባዋል፡፡ ቤታችንን አጥብቀን አልጠበቅንም፡፡ ቤታቸውን ሳይዘጉ ሰው ሌባ ይላሉ የሚለው ዓይነት ትዝብት እንዳይመጣ አስቀድመን የራሳችንን ቤት ለመጠበቅ መቆም አለብን፡፡

# በእውኑ ከአንድ ሰ/ት/ቤት ያሉ እኅቶችና ወንድሞች መጋባት አይችሉምን?

## ክፍል ሁለት

የተወደደዳችሁ አንባብያን የዚህን ጽሑፍ የመጀመሪያ ክፍል ከዚህ በፊት በነበረው እትም ላይ ማቅረባችን ይታወሳል። ቀጣዩንና ሁለተኛውን ክፍል ደግሞ እነሆ

### ሠ. ከሥነ ልቡና አንጻር

ትዳር ምንም እንኳን በእግዚአብሔር ፈቃድ የሚከናወን ቢሆንም በባለጉዳዮችም ብዙ ሊታሰብበት የሚገባ ከእግዚአብሔር የተሰጠ ነጻ ፈቃድ አለ። ከዚህ አንጻር ሁለቱ ተጋቢዎች የሥነ ልቡና ብስለት ሊኖራቸው ይገባል። ሚስትም ከጊዜያዊው ሥጋዊ ፍላጎት ባሻገር ሚስት መሆን እችላለሁን? የሚለውን ጥያቄ መመለስ አለባት። ባልም እንዲሁ ለጊዜው ከተፈጠረበት የወንድነት ስሜት ባሻገር በትክክል ባል መሆን እችላለሁን። ከባልነት ጋር ተያይዘው የሚከሠቱ ችግሮችን መቋቋም እችላለሁን የሚሉትንና የመሳሰሉትን ጥያቄዎች ለመመለስ የሚያስችል ሥነ ልቡናዊ ብስለት ያስፈልጋል።

ትዳር ሁለቱ እርስ በእርስ ሊረዳዱበት፣ ከብቸኝነት ጋር ተያይዘው የሚፈጠሩ ችግሮችን ሊያቀሉበት ዘራቸውን ሊተኩበት የሚመሠረት ተቋም ነው። ይሁን እንጂ አንዱን ችግር ለመፍታት ሲባል ሌላ ጥያቄ አብሮ ይነሣል። ሰው ከብቸኝነት ለመላቀቅ ሲል የሚያመጣት ሚስት የራሷ የሆነ ጠባይ፣ ፍላጎት፣ አመለካከት ወዘተ. ይዛ ትመጣለች። ባልም ቢሆን እንዲሁ አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ቀድመው እንዳሰቡትና እንደ ተመኙት ላይገኝ ይችላል። ስለዚህ ከነዚህ ሁሉ ጉዳዮች ጋር ተይያዘው የሚነሡ ጥያቄዎችን ለማስተናገድ የሚያስችል ሥነ ልቡናዊ ብስለት ያስፈልጋል።

### ረ. ከምጣኔ ሀብት አንጻር

ትዳር በእግዚአብሔር ፈቃድ የሚመሠረት ተቋም መሆኑን ማንም ሊዘነጋው አይገባም። ይሁን እንጂ በእምነት ካለመብሰልም፣ የትዳርን ምንነትና ተያያዥ ጉዳዮችን ባለመረዳትም አንዳንድ ጊዜ ደግሞ አስፈላጊ ከመሆኑም የተነሣ በገንዘብ ምክንያት የብዙ ሰዎች ትዳር ሲፈርስ ይስተዋላል። ጉዳዩን ግልጽ ለማድረግ ለምሳሌ ጥንዶች ሁለቱም ገና በትምህርት ላይ እያሉ ማለትም የወር ገቢ ሳይኖራቸው ወደ ትዳር እንምጣ ቢሉ የዕለት ጉርስ የዓመት ልብስ ያስፈልጋል፤ ከዚህ ጋር ተያይዞ ልጅ ይመጣል፤ የወር ወጪ ይጨምራል ስለዚህ ይህን ሁሉ ከግምት በማስገባት ቀድሞ ማሰብ ይገባል።

እኅታችን ከላይ የዘረዘርናቸውን ጉዳዮች ከሞላ ጎደል አሟልተሻል። የእምነት ጽናትሽን ማወቅ ባይቻልም በሌሎች ነገሮች ግን ወደ ትዳር የሚያስገቡ ነገሮች አሉሽ። ይሁን እንጂ የሰ/ት/ቤታችሁ ሕግ ደግሞ እሽ ለማለትም እምቢ ለማለትም አስጨንቆሻል። አሁንም ለዚህ ጭንቀትሽ መልስ ከመስጠታችን በፊት የሥርዓትና የመተዳደሪያ ደንብ የሚወሰንበትን ምክንያት፣ ሌላ ሰ/ት/ቤት መሄድ፣ ከነአካቴው ከአገልግሎት መቅረት፣ ወዘተ. . . የሚሉ ጉዳዮችን ደግሞ እንደሚከተለው እንመለከታለን።

### ሕጉ የወጣበትን ምክንያት ማጥናት

ሕግ ወይም ሥርዓት አጠቃላይ ቤተ ክርስቲያንን አንድ የሚያደርግ እንዳለ ሁሉ በየአጥቢያውና በየገዳማቱ፣ በእያንዳንዳችን ቤት ሳይቀር ይወሰናል። በየአንዳንዱ አጥቢያ፣ በየአንዳንዱም ገዳም፣ በየአንዳንዱም ቤተሰብእ የሚወሰን ሥርዓቶች ለተወሰነበት ቦታ ብቻ እንጂ ለሌላው ሕግ አይሆኑም። ለምሳሌ በአንድ ገዳም መነኩሴ ብቻ ነው የሚቀድስበት የሚል ሕግ ቢኖር ያ ሕግ ለዚያ ገዳም ብቻ እንጂ ለሁሉም ገዳማት አይደለም። እንደ አጠቃላይ ቤተ ክርስቲያንን አንድ የሚያደርጋት ሕግ ቀድሶ ቅዱስ ሥጋውን ክቡር ደሙን ለምእመናን ማቀበል፣ መባረክ ሥልጣነ ክህነት ላለው ብቻ የሚቻል መሆኑ ነው። ከዚያ ውጭ ግን መነኮሳት ብቻ ይቀድሱ፣ ባለሕግ ካህናትም ይቀድሱ የሚለው ሕጉ ለተወሰነበት ገዳም ብቻ የሚያገለግል ነው።

እንደዚሁም ሁሉ ማንም ሰው በጋብቻ ተወስኖ መኖር ሲፈልግ ቢቻል በሥርዓተ ተክሊል ደግሞ ለሰው ሁሉ አይቻልምና በሥርዓተ ተክሊል ካልተቻለ በመዓስባን በቤተ ክርስቲያን ሥርዓት መጋባት ሁሉንም አንድ የሚያደርግ ሥርዓት ነው። በቀጥታ ከተነሣው ጥያቄ ጋር ለማያያዝም መጋባት የሚችሉና መጋባት የማይችሉ በግልጽ በፍትሐ ነገሥት ተጽፏል፤ይህም የሥጋ ዝምድና፣መንፈሳዊ ዝምድናም ካለ ለምሳሌ የክርስትና እናት፣ የክርስትና አባት በመሳሰሉት ከተገናኙ፣ የጋብቻ ዝምድና፤ በሞግዚትነት ከቤት አድጎ/ አድጋ ቤተ ሰብ ከሆኑ፤ መጋባት አይችሉም። (ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ ፳፬፣ ፰፻፵፪-፰፻፰፩ ይመልከቱ)

ከዚህ ውጭ ግን በአንድ ሰ/ት/ቤት፣ በአንድ ማኅበር፣ በአንድ ቤ/ክ ወዘተ. የሚሉት ጉዳዮች ሕጉ ለተወሰነበት ቦታ ብቻ የሚያገለግል ነው እንጂ ለሁሉም አይደለም። ከምንም በላይ ቤተ ክርስቲያን የምታስተምረውን በዚህ መልኩ ከገለጽን ሰ/ት/ ቤቶች፣ ጽዋ ማኅበራት ለምን እንዲህ ያለ ሥርዓት ይደነግጋሉ የሚለውንም አብሮ ማየት ያስፈልጋል፤ በአብዛኛው ሰ/ት/ቤት የሚስተዋሉትን ችግሮችና እንዲህ ያለ ሕግ ለመወሰን የሚያስገድዳቸውን ጉዳይ እንደሚከተለው እንመለከታለን።

**ሀ. ሥርዓቱን ስለማይጠብቁ፡-** ቤተ ክርስቲያን በዕድሜ፣ በጾታ፣ በዘር፣ በቀለም፣ በጎሣ ወዘተ. ሳትለይ ሰው ሁሉ ወደ እግዚአብሔር እንዲቀርብ ትጣራለች ዕለት ዕለት ወደ እርሷ ለሚመጡትም አስፈላጊውን አገልግሎት ሁሉ በመስጠት፤ በአርባና በሰማንያ ቀናቸው ከማኅፀነ ዮርዳኖስ ከአብራከ መንፈስ ቅዱስ ተወልደው፣ በጸጋ መንፈስ ቅዱስ ታትመው፣ ለመንግሥተ ሰማያት እንዲበቁ ታደርጋለች። ቤተ ክርስቲያን ልጆቿን ከምታስተምርባቸውና ለመንግሥቱ እንዲበቁ ከምታደርግባቸው መንገዶች መካከል አንዱ ደግሞ የሰንበት ትምህርት ቤት ነው።

ይሁን እንጂ ሰዎቹ የቤተ ክርስቲያንን መሠረታዊ አስተምህሮና ዓላማ ባለመረዳት ወደ ቤተ ክርስቲያን ሲመጡ ልዩ ልዩ ፍላጎቶቻቸው ይከተሏቸዋል፤ ለማሟላትም ያስቡ ይሆናል። በዚህ ምክንያት ጋብቻ ሥርዓቱን እንዳያጣ፤ ለአቅመ አዳምና ለአቅመ ሔዋን ደርሰው በሥርዓተ ተክሊል መጋባት ሲኖርባቸው በአቋራጭ በጊዜያዊ ስሜት ተነሣሥተው ለውድቀት እንዳይዳረጉ፤ ክብረ ንጽሕናቸውንም እንዳያሳድፉ፤ ከቤተ ክርስቲያን ሕግና ሥርዓት የወጣ ተግባርም እንዳያከናውኑ፤ እነዚህ ከላይ የተዘረዘሩት ችግሮችን ለመፍታት ምንም ዘላቂ መፍትሔ ባይሆንም በአንድ ሰ/ት/ቤት ያሉ እኅቶችና ወንድሞች አይጋቡም የሚል ሕግ ሊወጣ ይችላል።

በእርግጥ ልብ ሊባል የሚገባው ጉዳይ ይህ ዘላቂ መፍትሔ ሊሆን ይችላል ወይ? የሚለው ነው። ምክንያቱም ልጆች የቤተ ክርስቲያንን መሠረታዊ አስተምህሮ እስካልተረዱ ድረስ ይህ ሕግ ብቻውን አይመልሳቸውም፤ ሲፈልጋቸው አገልግሎቱን ትተው ይሄዱና እኛም ነበርንበት ይላሉ፤ ካልሆነም ደግሞ ለዚህ ዓለማ ብለው ወደ ሌላ ሰንበት ትምህርት ቤት ይዘዋወራሉ። ይህ ደግሞ በራሱ ቤተ ክርስቲያን በማታስተምረው ትምህርት እንድትተች በር ከመክፈት በዘለለ ዘላቂ መፍትሔ ሊያመጣ አይችልም።

**ለ. ለሌላም መሰናክል ስለሚሆኑ፡-** ከላይ እንደተገለጸው ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያንን አለመጠበቅ አንዱ የትችት ጉዳይ ነው። ከዚህ በተጨማሪ በርካታ ሰዎች በሚሠሩት ኀጢአት ሌላውንም ሰው ይዘው ይወድቃሉ እንጂ ራሳቸው ብቻ አይደለም የሚወድቁት፣ ወጣቶች ወደ ሰንበት ትምህርት ቤት ሄደው ያልተገባ ሥራ ከሠሩ፣የሚመለከታቸው ሰው በእነርሱ ይሰናከላል። ቤተ ክርስቲያንን የቅድስና ማግኛ ሳይሆን ያልተገባ ሥራ የሚከናወንባት አድርጎ እንዲረዳት ይሆናል ። ስለዚህ በእንደዚህ ያለ ተግባር ተሰማርተው ለሌላ ሰው መሰናክል እንዳይሆኑ ሲሉ ችግሩን ከማቅለል አንጻር በዚያው በሰ/ት/ቤት ብቻ የሚሠራ መተዳደሪያ ደንብ ይወሰናል።

በቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ ኀጢአት ሠርቶ ከክብር መዋረድ ብቻ ሳይሆን ለሌላው መሰናክል መሆንም ከባድ ኀጢአት ነው። መድኃኔዓለም ክርስቶስ በሚያስተምርበት ወቅት መሰናክልን በተመለከተ "መሰናክል ግድ ሳይመጣ አይቀርም፤ ነገር ግን መሰናክሉን ለሚያመጣው ወዮለት፤ ከእነዚህ ከታናናሾቹ አንዱን ከማሰናከል ይልቅ የወፍጮ ድንጋይ በአንገቱ ታስሮ ወደ ባሕር ቢጣል ይጠቅመው ነበር" (ሉቃ.፲፯፣፩-፪) በማለት ሰውን ማሰናከል ምን ያህል ከባድ ኀጢአት እንደሆነ አስተምሯል። በመጽሐፍ ቅዱስ በሠሩት ኀጢአት ራሳቸው መቀጣታቸው ሳያንስ ለሌላ መሰናክል መሆናቸው ዕዳ በደላቸውን ያበዛባቸው በርካታ ሰዎችን እናገኛለን። ለማሳያ ያህል አንድ ምሳሌ እንመልከት።

አፍኒንና ፊንሐስ፡- የኤሊ ልጆች አፍኒንና ፊንሐስ ሕዝቡን እንዲመሩ እግዚአብሔርን እንዲያመስግኑ ተሹመው ሳለ ከተሾሙበት ዓላማ ወጥተው የማይገባ ሥራ በመሥራታቸው እግዚአብሔርን አሳዝነው፣ ለሕዝቡ መሰናክል ሆነው፣ ለታቦተ ጽዮን መማረክ ምክንያት ሆነዋል። በዋናነት የሠሯቸው መጥፎ ተግባራትም የሚከተሉት ነበሩ። ሙሴና አሮን የሠሩት በመጀመሪያው ሰዓተ ሌሊት አብርተው በመጀመሪያው ሰዓተ መዓልት የሚያጠፉት የመብራት ማብራት ሥርዓት ነበራቸው። ይህን አስቀርተዋል። ሁለተኛ ከተሠዋው መሥዋዕት ቀድሞ ለሊቀ ካህናቱ ይሰጥ የነበረውን ሥርዓትም እንዲሁ አፍርሰዋል። ሦስተኛውና ከዚህ የሚከፋው ደግሞ ወደ ቤተ እግዚአብሔር ከሚመጡት ሴቶች ጋር የነውር ሥራ ይፈጽሙ ነበር። በዚህም ምክንያት ሴቶችም ይህንንማ ከቤታችንስ መች እናጣዋለን ብለው ወደ ቤተ እግዚአብሔር የማይሄዱ ሆነዋል። ወንዶችም ሴቶቻችን ወደ ቤተ እግዚአብሔር ሄደው ተሳልመው በረከት ተቀብለው እንዲመጡ እንጂ ያልተገባ ሥራ ሊሠሩማ ከሆነ አንሰድም ብለው የሚያስቀሯቸው ሆነዋል፤ በዚህም የማያዳግም ቅጣት ተቀጥተዋል። (፩ኛሳሙ.፪፣፲፪-፳፮)

ዛሬም የቤተ ክርስቲያንን መሠረታዊ ትምህርት በጥልቀት ያልተረዱ ብዙ እኅቶችና ወንድሞች ወደ ሰ/ት/ቤት በድንገት ገብተው የቤተ ክርስቲያንን ሥርዓት ባልጠበቀ መልኩ ሕይወታቸውን ወደማይገባ የኀጢአት ሥራ እንዳያስገቡ በአንድ ሰ/ት/ቤት አገልግለው በረከትን ሊወርሱ ሲገባቸው፣ በትዳር መቀደስ ሳይሆን በዝሙት እንዳይሰናከሉ፤ ለቤተሰቦቻቸው ዕጥፍ ሸክም እንዳይሆኑ፤ በእነሱም ሥራ ምእመናንን እንዳያሰናክሉ፤ ወላጆችም በልጆቻቸው እንዳያፍሩ፤ በአንድ ሰ/ት/ቤት ያሉ አገልጋዮች መጋባት አይችሉም የሚል የቅድመ መከላከል ውሳኔ ቢወስኑ ተገቢ ነው ለማለት ያስደፍራል።

ስለዚህ በመጀመሪያ የተሄደለትን ዓላማ በአግባቡ መረዳት ያስፈልጋል። ቀጥሎ እግዚአብሔር የሰጠን አንዱና ተቀዳሚው ጸጋ ነውና ቤተ ክርስቲያን በምትፈቅደው መልኩ ጋብቻቸውን ቢፈጽሙ ክፋት የለውም እንዲያውም አርአያነትም ነው። ይሁን እንጂ አንድ ችግር ለመፍታት ሌላ ችግር መፍጠር ግን ተገቢ አይደለም። ለምሳሌ አንድ እኅት ያደገችበት ሰ/ትቤት ነው። አንድ ሌላ ወንድምም እንዲሁ ያደገበት ሰ/ት/ቤት ነው። ምን አልባትም ሌላ የመተዋወቂያ ዕድል እና አጋጣሚው ላይኖራት ይችላል። ይህ ብቻ አይደለም እግዚአብሔር ለእርሱ ያላትን ሴት ያዘጋጀለት ከዚሁ ሰ/ት/ቤት እንደሆነስ? ለእርሷም እንዲሁ? ስለዚህ ከላይ በተገለጸው መልኩ የቤተ ክርስቲያንን ሥርዓት መጠበቅ፤ እስከ ጋብቻ ጊዜ ድንግልናን መጠበቅ፤ በእጮኝነት ወቅትም ከጊዜያዊ ስሜት ተገድቦ ለምክክር የሚያጠፉት ጊዜ ቢኖር እንኳን ሰዎችን ሊያሰናክል በማይችል መልኩ ማከናወን፤ በተለይ ወደ ቤተ ክርስቲያን ለአገልግሎት ሲመጡ አገልግሎቱን በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ ብቻ በማተኮር በእጮኝነት ስሜት የሚስተዋሉ ነገሮችን በማስተካከል መፈጸም ይችላሉ። ለዚህ ሲሉ ለምንስ ያደጉበትን ሰ/ት/ቤት ይለቃሉ? ለምንስ ከአገልግሎት ይሸሻሉ? ይህ ጉዳይ በሌሎች ሰ/ት/ቤቶችም ሊታሰብበት ይገባል።

ስለዚህ ሕጉ የወጣው ለዚሁ ሰንበት ትምህርት ቤት እንጂ መሠረታዊ የቤተ ክርስቲያን ትምህርት ስላልሆነ ሊፈጠር የሚችለውን ችግር ለመከላከል ይህ ብቸኛ መፍትሔ አይደለምና በሚመለከተው አካል ሕጉ መታየትና መስተካከል ይኖርበታል። ከዚህ በላይ ሕፃናትን ከመጀመሪያው ጀምሮ መሠረታዊ ትምህርት ማስተማር፤ ወጣ ገባ የሚል የሰንበት ተማሪ ካለ ከወላጅ ጋር በመነጋገር በትኩረት የሚያድግበትን መስመር መዘርጋት፣ ቤተ ክርስቲያን በመሠረታዊ የማታስተምረውን ትምህርት እንደቤተ ክርስቲያን መደበኛ ትምህርት እየቆጠርን ለልጆቿ የማትመች፣ ሕግ የምታጠብቅ እያልን የሌላትን ስም ለመስጠት መንገድ የሚከፍቱ ጉዳዮችን በአጭሩ መፍታት ይኖርብናል።

በአጠቃላይ እኅታችን ላነሣሽልን ጥያቄ በድጋሜ በእግዚአብሔር ስም እያመሰገንን ሕጉ በአንዳንድ ሰንበት ትምህርት ቤቶች የሚወጣ የውስጥ መተዳደሪያ ደንብ እንጂ የቤተ ክርስቲያን መሠረታዊ አስተምህሮ አለመሆኑን መረዳት፣ በቤተ ክርስቲያን የሚወጡ መመሪያዎችና ደንቦች ከታላቁ መጽሐፍ ቅዱስና ከፍትሐ ነገሥት ወ.ዘ.ተ የወጣ መሆን የለበትም ቅዱሳት መጻሕፍትን መሠረት ያደረገ መሆን ይገባዋል። በዚህ ምክንያት ልጆች ከአገልግሎት የሚርቁ፣ የመኖሪያ ቦታ ለውጥ ሳያደርጉ ለዚህ ተግባር ብቻ ብለው ሰንበት ትምህርት ቤት የሚቀይሩ ከሆነ ይህ መጀመሪያ የወጣው ሕግ ሁኔታዎችን አገናዝቦ እንደወጣው ሁሉ ይሽኛውም ሕግ የሚስተካከልበትን መንገድ መፍጠር ይገባል እያልን፤ ችግሩ የአንድ የግለሰብ ብቻ ሳይሆን በተመሳሳይ የሌሎችም ችግር(ጥያቄ) ሊሆን ይችላልና ዘላቂ መፍትሔ ማምጣት ያስፈልጋል። አንቺ ግን የቤተ ክርስቲያንን ሥርዓት ጠብቀሽ፤ ከአባቶች ጋር ተመካክረሽ እግዚአብሔርን በጸሎት ጠይቀሽ ማግባት የምትችይ መሆኑን መግለጽ እንወዳለን። እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያንን፣ ምእመናንን፣ ይልቁንም ለፈተና ቅርብ የሆኑ የወጣቶቹን ሕይወት በቸርነቱ ይጠብቅልን አሜን።